« ገጠር እልሽ ልጄ ፤ የገጠሩ ባለቤት ቢፈቅድልሽ አይደል ፣ ለጉልበቱማ ሠርቶ መብላቱን የሚጠላ ማን አለ ? »

ድንገት ከፊት ለፊታቸው ፣ ሩቅ ከማይባል ስፍራ የሆነ ነገር ዓይናቸውን ሰረቀው ። ከሲታው ሰውነታቸው መዝለፍለፍ የጀመረ እጃቸውን መሸከም አቃተው ። ግርግር ይታያል ፤ ሰዎች ይተራመሳሉ ።

« ነይ እስቲ እንሂድ ። ዛሬ ደግሞ ምን ተፈጠረ ? ወደፖሊስ ጣቢያ እንዳይሆን የሚሄዱት . . . » አሉና ፍጥነት ጨመሩ ። ኅስቋላ ቤቶችን አልፈው ዙርያውን በግንብ የታጠረ ፣ መሀሉ ላይ ሰንደቅ ዓላማ የሚውለበለብበት ግቢ ሲደርሱ ካዩት ትርምስ ጋር ተገጣጠሙ ። አንድ ሰውነቱ ሁሉ ደም የለበሰ ሰው ፖሊሶች ወደ ጣቢያ ያዳፋታል ። ልጅቷ « ምን ሊያደርጉት ነው ? . . . » ስትል ጠየቀች ድንጋጤና ፍርሃት እየናጣት ።

« እኔ ምን አውቃለሁ ብለሽ ነው » ሲሉ እራሳቸውን በመነቅነቅ መለሱላት ። ቢሆንም ሁኔታው ከቁጥጥራቸው ውጭ ነበር። ካጠገባቸው የሚገኙትን ሰዎች እየገፋፉ ሰርስረው ወደፊት አለፉ ።

« መጥኔ ለሚስቱና ለልጆቹ ። ምን ይሉ ይሆን ? እዚህ መሀል እኮ ይኖሩ ይሆናል ? » ከነፋሱ ጋር የሚታገለውን ነጠላቸውን ወደ አፋቸው እያስጠጉ ። ሳያስቡት እንባቸው ከዓይኖቻቸው እርግፍ እርግፍ አለ ። ወዲያው በነጠላቸው ጫፍ እንባቸውን እየጠራረጉ « በይ ነይ እንሂድ ይህ ዓይነቱ ቦታ ላንቺ ለእምቡጧ ጥሩ አይደለም፣ እኛ የሰራነው ግፍ ለልጆቻችን ተረፈ ። » አሉና የሕሊናን እጅ በመጎተት ከተሰበሰበው ሰው መሀል ለመውጣት ሞከሩ ። ልጅቷ ለመውጣት ፍላጎት አልነበራትም ።

« ለምን መጥፎ ነገር ማየት አባቴም እርስዎም ትከለክሉኛላችሁ ? ማየት ለመማር ይጠቅም የለ ? » ስትል ጠየቀች ።

« አዬ ልጄ ! መጥፎን ነገር ማወቁ ለማንም ቢሆን ጥሩም አይደል ፡፡ ሁሉንም ሰማወቅ እንደምትፈልጊ ይገባኛል ፡፡ የልጅነት ነገር ሆኖብሽ ነው እንጂ » አሉና ድምፃቸውን ውጠው « ክፉና ደጉን ለይቶ ማወቅ አይከፋም ነበር ፣ ከበስተኋላው ተንኮል የማያስተምር ቢሆን ኖሮ ፡፡ » ሲሉ በውስጣቸው አጉተመተሙ ፡፡

« አባቴ ሁልጊዜ እንደሱ ጎበዝና ደፋር ፣ እውነት ፈላጊ እንድሆን ይመክረኛል ፡፡ ነገር ግን እንደ አባቴ ጎበዝ ፣ ደፋርና ሀቀኛ ይገኝ ይሆን ? እቴቴ በላይነሽ ፡፡ »

« እንደ አባትሽ ደፋር ፣ ጎበዝና ሀቀኛ አይገኝም » እያልዋት ጥቂት ርቀት ከሄዱ በኋላ ፊት ለፊታቸው የሚታየውን ትልቅ መስኮት እየጠቆሙ ይኸው « የመጣንበት መድኃኒት ቤት ፣ እኔ ገብቼ ለአባትሽ የሚሆን መድኃኒት ልጠይቅ ፡፡ አንቺ ደግሞ ከዚያ ሱቅ ሂጂና ቡናና ስኳር ገዝተሽ ነይ ፡፡ ያዥ ይሄን » ብለው ሃምሳ ሳንቲም ሰጧት ፡፡ ልጅቷ ወ/ሮ በላይነሽን በፍቅር ዓይን እያስተዋለች « እቴቴ በላይነሽ በጣም ተቸገሩ አይደል ? » ለጥያቄዋ መልስ አልጠበቀችም ፤ ወደተባለው ሱቅ በሩጫ በረረች ፡፡ ብዙም ሳትቆይ በወረቀት ሁለት ትንንሽ ጥቅሎችን ይዛ ተመለሰች ፡፡

ወ/ሮ በላይነሽ ሀዘን በተሞላው ድምፅ « አገኘሽ ልጄ » ፀጉሯን እየደባበሱ ጠየቋት ፡፡ እሷም ማግኘቷን ጭንቅላቷን በማወዛወዝ ገለፀችላቸው ፡፡

« በይ እንግዲህ ወደማረፊያችን ተመልሰን ቡናችንን አፍልተን ከአባትሽ ጋር እንጠጣለን ፣ አባትሽ ቡና በጣም ይወዳል ፡፡ ቡና ሲጠጣ ከበሽታው ትንሽ የተፈወሰ ይመስለዋል . . . » ብለው የጀመሩትን ሳይጨርሱ ልጅቷ ከአፋቸው ነጠቀቻቸው ፡፡

« አባቴ ቡና ከጠጣ ሦስተኛ ቀኑ ነው ፡፡ ቡና ሳፍላ ብዬ ስጠይቀው ፊቱ ይኮሳተራል ለምን እንደሆነ አልገባኝም » እንባዋ



ታገላት ፣ ሳግ ተናነቃት ፡፡ ወ/ሮ በላይነሽ ፊት የነሷት መሰሉ ፡፡ ዝም ተባብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ ፡፡

« ሕሊና » አሉዋት ቤታቸው አካባቢ ሲደርሱ ፤ « ጥሩ ልጅ ነሽ ፡፡ አሁን ወደ ጉልት ሄደን የሚበላ ነገር ገዝተን ወደ ቤታችን እንገባለን ፡፡ »

« እኔም ጉልት መሄድ እፈልግ ነበር ፡፡ እዛ ሁሉም ነገር ይገኛል ፡፡ ስኳር ድንች . . . አይገኝም እቴቴ በላይነሽ ? »

« ገንዘብ ላለው ሰማይ ቅርቡ ነው ሲሉ አልሰማሽም ፡፡ ገንዘብ ካለ እንኳንስ ስኳር ድንች የሰው ነፍስም ይገኛል ፡፡ . . . ስኳር ድንች ፈለግሽ እንዴ ? »

መፈለጓን ቅር ባለ ስሜት በመግለጽ ቀና ብላ ወ/ሮ በላይነሽን አስተዋለች ፡፡ ገንዘብ ሳይኖራት የምትፈልገውን በመናገሯ አሳፈራት፡፡

« ምን አለበት እቴቴ በላይነሽ እንደ እናቴ ማለት ናቸው » ብላ ራሷን ለማፅናናት ሞከረች ፡፡ እሳቸው የፈለገችውን ነገር ሁሉ ያደርጉላታል ፡፡ « ገንዘብ ከየት ያመጣሉ ? ሲጠየቅ የማይገባውን ነገር ነው ያነሳሁት » በእጇ ጥብቅ አርጋ ለያዘችው ዕቃ የምታወራ ትመስላለች ፡፡

« ዛሬ አባቴ አምሽቶ እንድሰራ የሚፈቅድልኝ ይመስልዎታል? እቴቴ በላይነሽ ፣ አባቴም ሥራ ካቆመ ቆየ ፣ እስከ መቼ ድረስስ በርስዎ ትክሻ ይኖራል ? ደግሞ ሥራውም ጠፋ ፡፡ ከእንግዲህ አባዬም ቶሎ የሚሻለው አልመሰለኝም » አለች ሕሊና ፡፡

« በይ አርፈሽ ተቀመጭ ! አባትሽ እንዲያውም ያንቺን በቤት ሠራተኝነት ላይ መሰማራት በጣም ነው የሚጠላው ፡፡ የሰው እጅ እንዳታዪ የሚያደርገው ጥረት ይህ ነው አይባልም ፡፡ ደግሞ የኔ ነገር ምን አደረኩላችሁ ! ምነው በቻልኩና አቀማጥዬ በያዝኳችሁ » እንደድንገት የሆነ ብርሃን ታያቸው « ለማንኛውም የነገውን ቀን

እንዴት እንደምናደርግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ተጨምሮበት በነገው ዕለት እናያለን » አሏት ::

* * *

ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ አንድ ገርበብ ብሎ የተዘጋ የቆርቆሮ በር ገፋ አድርገው ገቡ :: ወ/ሮ በላይነሽ ራሳቸው ላይ ጣል ያደረጉትን ነጠላ አውርደው « እንደምን ዋላችሁ » ሲሉ ከቤት ውስጥ ሲያንጎዳጉድ የቆየ ውሻ ሲወጣ በድንጋጤ ጮኹ ::

« ቸሩ እኮ ነው እቴቴ በላይነሽ ፤ ፈሩት እንዴ ? » ሕሊና ፈገግ ብላ ፣ ሳቋን አፍና ልታረጋጋቸው ሞከረች :: ወ/ሮ በላይነሽ ቤት ውስጥ መሬት ላይ ቡቱቶ ለብሶ የተኛውን ሰው መልከት አድርገው ፣ በእጃቸው የያዙትን ወረቀት ገለጡና « እንካ ቀና በል እስቲ ይሄን ዋጥ :: ትንሽ ቢያሽልህ » ብለው ሁለቱን ኪኒን እጃቸው ላይ አደረጉላቸው :: « ውኃ አምጭለት እስቲ » አሏት ሕሊናን ::

ከወለሉ ላይ የተዘረጉት ፣ በዒም የተወረሩ፣ ህመም ያጉሳቆላቸው አቶ የፊላ ከአንገታቸው ቀና ብለው ፤ የተሰጣቸውን ኪኒን ከወ/ሮ በላይነሽ እጅ ተቀብለው ወደ አፋቸው ወርወር አድርገው ከሕሊና በጣሳ የተቀበሉትን ውኃ እየተናነቃቸው ተጎነጩ ::

ወ/ሮ በላይነሽ የተረፈውን መድኃኒት ለሕሊና ሰጥተው ከቤት እንደወጡ ፤ ሕሊና መድሃኒቱን ለአባቷ እያሳየች « ይህን ሁሉ መድኃኒት ውጠህ ስትጨርስ ከበሽታህ ትፈወሳለህ አይደል አባብዬ ?» አለች ::

አቶ የፊላም የልጃቸውን ምኞት በደስታ የተቀበሉ ይመስል ፈገግ ሲሉ ፣ ልጃቸውም አፀፋውን በደስታ ስሜት መለሰችላቸው :: አጥንት ብቻ የቀረውን እጃቸውን ወጣ አድርገው በተኮማተሩ ጣቶቻቸው መድኃኒቱን ተቀብለው እንደ ትራስ በሚጠቀሙት የግንድ



እንጨት ሥር ወርወር አድርገው ቀስ ብለው ተመልሰው በግንዱ ላይ ራሳቸውን አሳረፉ ::

ሕሊና አባቷ ከተኙበት ወለል ፊት ለፊት ተቀምጣ ፊቷን በእጆቿ መሀል አስደግፋ ህዘን በተሞላበት ስሜት አባቷን ከላይ እስከታች ቃኘች :: አቶ የፊላ በደከመና በሰለለ ድምፃቸው « ሕሊና በዚህ ንፁህ አስተሳሰብሽ ላይ የተማርሽ ብትሆኚ ምንኛ የረካሁ በሆንኩ :: በድህነታችን ምክንያት በዘራችን የተማረ የለም :: አንቺን ለምኜም ፣ ለፍቼም ለማስተማር የነበረኝ ምኞት የላቀ ነበር ::

ግና ምን ያደርጋል ፣ አቅሙ ጠፋ ! የአቅም ማነስ . . . አቅም . . .» ሕሊና ልታስጨርሳቸው አልቻለችም :: እንባዋ እየተናነቃት እጃቸውን በእጆቿ እየዳሰሰች » አባዬ አንድ ቀን እግዚአብሔር ሲፈቅድ እማር ይሆናል :: እየለመንኩም ቢሆን እማራለሁ :: ነገር ግን ካንተ ተለይቼ ለመኖርም ለመማርም ምንም ሀሳብ የለኝም :: ለትምህርት ብዬ ከአንተ ተለይቼ ለመኖር ፈጽሞ አልፈልግም :: በዚህ ህመምህ ስለኔ መማር ያለመማር መጨነቅ የለብህም :: ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው :: » አባቷ የሕሊናን የልጅነት አንደበት በማለሳለልና እየበለለች መምጣቷን በማድነቅ ፣

« መማር ልጄ ማንንም አልጎዳም :: እኔ ላንቺ መከራ እንጂ ደስታን የማመጣ ሰው አልሆንኩም ፣ ሆኖም እንድትማሪ እፈልግ ነበር :: »

« አባዬ ከእንግዲህ እኔ ልጅ አይደለሁም :: የምትለው ሁሉ ይገባኛል :: . . . ምኞትህ ከሆነ ትምህርቴን ጊዜና ቦታ ሲያጋጥመኝ እማራለሁ » ስትል አባቷን ለማፅናናት ያህል ተናገረች ::

« ሕሊና ! ለመሆኑ አንድ አክስት እንዳለችሽ ታውቂያለሽ ?» የሆነ ተስፋ የሚያስቆርጥ ስሜት እየወረራቸው ፣ ለውነታቸው እየከዳቸው የሄደ መሰላቸው ::

« አዎ አንድ ቀን ነግረኸኝ ነበር » አለቻቸው ::

ቀስ ብለው ራሳቸውን በጃቸው ደገፍ አድርገው ክንዳቸውን መሬት ላይ በማሳረፍ « ሕሊና ! ሌላዋ አክስትሽ ደግሞ እዚህ ትልቅ ከተማ አለች » አሏት ::

« እዚህ ሀገር ? » አለች በመገረም :: እራሳቸውን በማነቃነቅ የአዎንታ ምልክት አሳይዋት ::

« ይህችኛዋ አክስትሽ ደግሞ የእናትሽ እህት ነች » አሏት ::

« የኔ እናት እህት የእውነት እዚህ ከተማ አለ ነው የምትለኝ? » አለቻቸው ::

« እዚህ በአቅራቢያችን ሳይሆን ትንሽ እራቅ ወዳለ ሥፍራ ነው » አሏት ::

« ግን እኛ ልናገኛቸው እንችላለን ? » ስትል በጉጉት ጠየቀቻቸው ::

« እኔ እንኳን . . ላያት አልችልም እኔን አትወደኝም :: ግን አንቺ ሄደሽ አግኚያት »

ሀዘን በተሞላበት አነጋገር « አንተን የሚጠሉ ከሆነ እኔም አልወዳቸውም . . . » የአባቷ አለመወደድ አክስቷን ለማወቅ የነበራትን ጉጉት አጨለመው :: አባቷ እጇን እየዳሰሱ ለስለስ ባለ አነጋገር « እኔን በመጥላቷ አትፍረጅባት :: ለጥላቻዋ ተመጣጣኝ ምክንያት አላት :: እናትሽን ወርቂቱን ጠልፌ እንድታገባኝ ያስገደድኳት እዚች አክስትሽ ጋር ትኖር በነበረበት ጊዜ ነው :: በዚህ ምክንያት አክስትሽ እናትሽንም ሆነ እኔን ሁለተኛ ዞር ብላ ለማየት አትሻም ነበር :: » ሲሉ ሊያስረዷት ሞከሩ ::

« እንግዲያውስ እኔንም ለማየት አይፈልጉም :: »

አባቷ የልጃቸው የወደፊት ሁኔታ እየታያቸው ለማግባባት ቢሞክሩም እሷ ባደረባት የጥላቻ ስሜት ላለመቀበል ጣረች ::

« አይ አንችንማ ብታይሽ አትጠላሽም »



« እኔ ደግሞ ከአንተ ተለይቼ እሳቸውን ለማየት አልፈልግም:: በዚህ ላይ ከሰሞኑ አንተ ታመህ በመተኛትህ ለእቴቴ በላይነሽ ለቤት ኪራይ የምንከፍለውና ለምግብ የሚሆነን ገንዘብ የለንም :: እንደምንም ብዬ የሚሰራ ሥራ ፈልጌ ገንዘብ ማግኘት አለብኝ :: እቴቴ በላይነሽ ይረዱኛል :: »

« ሰማሽ ሕሊና ! በየሰው ቤት እየተንከራተትሽ እንድትሰሪ አልፈልግም ፤ ከእንግዲህ በቃ ! በቃ ነው የምልሽ ! » ዓይናቸውን ከድነው እራሳቸውን እየነቀነቁ ቁጣ ባዘለ ስሜት « የኔና ያንቺ እህል ውኃ በዚህ ያበቃል » አሏት ::

« ለምን ? ምን አደረኩ አባባ ? » አለች ሕሊና በድንጋጤ ::

« . . . የኔ ሕሊና ከግርድና ሥራ የተሻለ ነገር ነው ላንቺ የምመኘው :: »

ቁጣቸው እየበረደ መጣ :: እንደ ትራስ በሚጠቀሙበት ግንድ ላይ እራሳቸውን አሳረፉ :: « እንዲህ ቁርጠኛ ከሆንክ ያኔ ወደ ነገርከኝ ያንተ እህት ወደ ሆነችው አክስቴ ብሄድስ ? » አለች ሕሊና ፍርሃት በተሞላው ቃል ::

እንደማጉረምረም ያለሳቅ በማሰማት ዓይናቸውን ጥቅርሻ ወደወረሰው ጣሪያ እየተመለከቱ « የእኔም ምኞት ነበር :: ምኞት ብቻ ሆነ እንጂ ! እሱማ ቢሆን . . . ነገር ግን . . . አይሆንም :: የኔ እህት ያለችበት ቦታ በጣም ሩቅ ነው . . . በዚህ ላይ እህቴ እኔ እንደምፈልገው ልታሳድግሽ ዕድሜዋ የሚፈቅድላት አይመስለኝም ፤ በአሁኑ ወቅት የኔ እህት ዕድሜዋ ወደሰባው እየተጠጋ ነው » አሉ ሀዘንና ሀሳብ በተቀላቀለው ስሜት ::

« . . . እም ዓይኖችሽ የደጓን እህቴን ዓይኖች ይመስላሉ :: ስሜትሽም እንደ እሷው ነው :: ያቺን ደግን የገጠር እህቴን መስለሽ ተፈጥረሻል :: እም የአባዋጅ ዘሮች በደማቸው ያስታውቃሉ . . . እናትሽ የስሜት ተገዥ አልነበረችም :: እናትሽ መልከ መልካም

ነበረች ፡፡ አንቺም እንደ እናትሽ መልከ መልካም ነሽ ፡፡ ፀጉርሽ የእናትሽን ይመስላል ፡፡ ፀጉርሽ ተባይ እንዳይፈጥር ተንከባከቢው ፣ ታጠቢው ፡፡

እናትሽ ፀጉሯን መታጠብ ትወድ ነበር ፡፡ . . . እናትሽ በጣም ደግ ሴት ነበረች ፡፡ በጣም ! በጣም ! . . . ! » ሀሳባቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከተሰየችው ባለቤታቸው ጋር ሄደ ፡፡ ብዙ በመናገራቸው ፣ ቶሎ ቶሎ መተንፈስ ጀምረዋል ፡፡

ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ ድምፃቸው እየራቀ መጣ ፡፡ ሰመመን ይዟቸው ወደ ጣር ዱካ አስጠጋቸው ፡፡ ሕሊና በጉልበቷ ተንበርክካ አባቷን በድንጋጤ ተመለከተች ፡፡ ጭንቀታቸው ሠላም ነሳት ፡፡ በወረቀት የተጠቀለለውን ኪኒን ከትራስጌያቸው አንስታ « አባዬ ፣ አባዬ ፣ እንካ ይሄን ዋጥ ያሽልሃል ፡፡ አባብዬ . . . ፡፡ » ልጅቷ የያዘችውን ነጫጭ ኪኒኖች ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ተመለከቱ ፡፡ መድኃኒቱን ሳይሆን ወ/ሮ በላይነሽን እንድትጠራ ተማፀኗት ፡፡

« እቴቴ በላይነሽ እቴቴ በላይነሽ ! » በማለት ደጋግማ ተጣራች በተደናገጠ ስሜት ፡፡

ወ/ሮ በላይነሽ በአካባቢው ባለው የወዳደቀ አጥር አጠገብ ስከሰል ማቀጣጠያ የሚሆን የረገፈ የባህር ዛፍ ቅጠል ይለቃቅሙ ነበር፡፡ ድንገት የሕሊና የድረሱልኝ ድምፅ ተሰማቸው ፡፡

ወ/ሮ በላይነሽ እየተጣደፉ ቤት ሲደርሱ አቶ የፊላ ከሞት ጋር ግብግብ ገጥመው ነበር ፡፡ ወ/ሮ በላይነሽን እንዳዩ ቀርበው እንዲሰሟቸው ምልክት አሳይዋቸው « ወ/ሮ በላይነሽ . . . እህ . . . እህ . . . እህ . . . የሕሊና . . . እህ . . . እናት . . . እህ . . . እህ እናት እህት . . . አቃቂ በለቃ . . . እህ . . . እህ . . . የቡና . . . ቤት ባለቤት . . . ባለቤት . . . ለሷ . . . ስጡልኝ . . . ሕሊና ትምህርት . . . ትምህርት አባይነሽ . . . ሕሊና መማር . . . መማር . . . መማር . . . » እያቃሰቱ የቻሉትን ያህል ለማስረዳት ሞከሩ ፡፡



ሕሊና እየተቆራረጠ የሚወጣውን የአባቷን ቃል ከወ/ሮ በላይነሽ ጎን ቀረብ ብላ ተንበርክካ ለመስማት ሞከረች ፡፡

*    *    *

ሕሊና ከአባቷ ሞት በሁዋላ በነበሩት ተከታታይ ቀናት ስለተፈጸሙት ሁኔታዎች እጅግም አታስታውስም ፡፡ ጎኑዋ ላይ ከሚሰማት ህመምና እንደብኸርታ ከሚታያት የአባቷ መቃብር ውስጥ ሳትወድቅ እንዳልቀረች ትገምታለች ፡፡ ከዚህ በቀር እንደዋዛ አባቷ ከጎንዋ የሉም ፡፡ አላፊ አግዳሚው ከንፈሩን የሚመጥላት ምስኪን ሆናለች ፡፡ ስለምንም ነገር ማሰብ አልቻለችም ፡፡ ተስፋ ቆርጣ ሀሳቧን ሁሉ ለወ/ሮ በላይነሽ ትታ ይሆን ? ያሰኛል ፡፡ በእርግጥ ወ/ሮ በላይነሽ አሳቢዋ ፣ ለወደፊት ህይወቷ ተጨናቂ ነበሩ ፡፡

አንድ ቀን ወ/ሮ በላይነሽ ከአንድ ሠፈርተኛ መነኩሴ ጋር ሆነው ሕሊናን ወደ አክስቷ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት መሄድ እንዳለባት ገለጹላት ፡፡ ሕሊና ግራ ተጋብታ ዓይኖችዋን ከወዲያ ወዲህ እያንከባለለች ሁለቱን ሴቶች ተመለከተች ፡፡

« እውነቷን ነው ፡፡ ይህ እንዲሆን አደራ ያለው አባትሽ ነው፡፡ ያ ባይሆን የዚህ ሰፈር ሰዎች ተጋግዘን አንቺን እንደገዛ ልጃችን ለማሳደግ ባልሰነፍንም ነበር ፡፡ የሆነ ሆኖ የአባትሽ ፣ የሙት ቃል በምድርም በሠማይም ያስጠይቃል መከበር አለበት » አሏት መነኩሴዋ የወ/ሮ በላይነሽን ሀሳብ በመደገፍ ፡፡

« አባትሽ ከመሞቱ በፊት ወ/ሮ አባይነሽ ዘንድ ሽማግሌ በመላክ እንዲታረቁት መማፀኑን ነግሮኛል ፡፡ በዚህ ላይ ወ/ሮ አባይነሽ የተነገረላቸው ሀብታም ነጋዴ መሆናቸውን ሰዎች ሁሉ ያወራሉ ፡፡ ላንቺም ከሳቸው ጋር መሆኑ ሳይሻልሽ አይቀርም ፡፡ ትምህርትሽንም መማር ትችያለሽ » ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽም ሀሳቡን አጠናከሩ ፡፡

መቀነታቸው ላይ የነበረውን ቋጠሮ ፈትተው አራት ቀያይ የብር ኖት አነሱና « ያዥው ፤ ለዕዝንሽ ሠፈርተኛው ያዋጣልሽ ብር ነው ። ትንሽም ቢሆን ይጠቅምሻል » አሏት ። ሕሊና የእዝን የሚሰውን ቃል ገና እንደሰማች የሆነ ነገር ውስጧን ሲቆርጠው ተሰማት ። የአባቷን ሞት ዕዝን መቀበል በጣሙን ቀፈፋት ፤ ዘገነናት ። ወ/ሮ በላይነሽ እጅ እንዲቀር ተመኘች ። ሴትዮዋ ግን ላለመቀበል አንገራገሩ ።

« እዚህ አብረን ስንኖር የቤት ኪራይና የምግብ እንዳልከፈልንዎት ያውቃሉ ። አባዬ ቢኖር ከዚህ የበለጠ ይከፍልዎት ነበር ። በአባቴ አፅም ይዤዎታለሁ ! ይተውኝ » አለቻቸው ።

በአባቷ ትዝታ ህመሟ የሚያገረሽባት ስለመሰላቸው ሁኔታዋን ለማረጋጋት ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ ከብዙ ማመንታት በኋላ ከሕሊና ብሩን ተቀብለው « በአባትሽ አፅም ከያዝሽኝ ምን አደርጋለሁ ። ባይሆን ለአባትሽ የተዝካር ማውጫ ይሆናል » አሉና ብሩን በመቀነታቸው መልሰው ቋጠሩ ። ሕሊና አቅሟ በፈቀደላት መጠን አባቷን ከዕዳ ነፃ በማድረጓ ደስታ ተሰማት ። ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ የአባቷን ልብስና መጥረቢያውን ከራሷ ዕቃ ጋር በማዳበሪያ መሳይ ከረጢት ቋጥራ ለማይቀረው ጉዞ ተዘጋጀች ።

ወ/ሮ በላይነሽም በገቡት ቃል መሠረት አክስቷ ዘንድ ሊያደርሷት ተነሱ ። ከበሩ ወጣ እንዳሉ ፣ የሠፈሩ ሰዎች ከንፈራቸውን በሀዘኔታ እየመጠጡ ፣ ጉንጯን አገላብጠው እየሳሙና እየመረቁ ተሰናበቷት ። በእጇ ያንጠለጠለችውን ከረጢት ታዳጊዎች ተሸክመው መኪና ተራ ድረስ ተከተሏት ።

የአቃቂ አውቶቢስ ጥቂት ካስጠበቃቸው በኋላ በቦታው ቆሟል። ሕሊና አብሮ አደግ ጓደኞችዋ አጠገቧ ቆመው ዓይን ዓይኗን ሲያዩ እንባዋ አቀረረ ። የልጅነት ስሜቷ ያለችበትን ሁኔታ አስረሳት። ዓይኖችዋን ከልጆቹ ላይ ሳትነቅል በደመነፍስ ወደ አውቶብስ ስትገባና



አውቶብሱ ሊንቀሳቀስ አንድ ሆነ ። በዚሁ መሀል እግሯ ተንሸራቶ በመውደቅ ላይ ሳለች በሩ አጠገብ ቆሞ የነበረ ወጣት እጇን ይዞ አዳናት ። በወቅቱ የምትተነፍሰው ቃል አልነበራትም ። አንገቷን አቅንታ እንዳትወድቅ ለታደጋት ወጣት ምስጋናዋን ገለፀችለት ። ወ/ሮ በላይነሽ በመካከል ፣ ሕሊና ከቀኛቸው ከመውደቅ የጠበቃት ልጅ ከግራቸው በኩል እንደተቀመጡ አውቶቢሱ ወደ አቃቂ ከተማ መጣደፉን ቀጠለ ።

ሁኔታው ለወ/ሮ በላይነሽም ሆነ ለሕሊና ሁለት ገፅታ ነበረው። ሁለቱም መለያየቱ ጨንቋቸዋል ። ግን ደግሞ መለያየት አለባቸው ። ከወሬ እንደታወቀው የሕሊና አክስት ሀብት ያላቸው በመሆናቸው የሕሊና ህይወት ይለወጣል ። በዚህ ደግሞ ወ/ሮ በላይነሽም ይጠቀማሉ ፤ ሕሊና አትረሳቸውም ። በእንዲህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ሆነው ብዙ ተጓዙ ። አቃቂ ከተማ በመቃረብ ላይ እንዳሉ ሕሊና የሆነ ጥያቄ ለወ/ሮ በላይነሽ ሰነዘረች ።

« እቴቴ በላይነሽ ፤በቃ የምኖረው አቃቂ ነው ማለት ነው?» አለቻቸው ። ቤቱ ከተገኘ የመለያየታቸው ነገር አሳሰባት ። ወ/ሮ በላይነሽ ስሜቷ የሳቸውም ስለነበር ጥያቄዋ ውስጣቸውን ይበልጥ አሸበረው ። ፊቷን ላለማየት እየጣሩ ፤

« ምን አለበት አቃቂ ሩቅ አይደል ። እኛም እየመጣን እንጠይቅሻለን ። አንቺም ትመጫለሽ ። በእርግጥ የአባትሽ የአደራ ቃል ባይሆን ከኔ ጋር አብረን ብንኖር እንዴት ደስ ባለኝ ። ቢሆንም የአባትሽ ቃል ይበልጣል ። አባትሽ የሆነ ነገር ባያስብ ይኽን እያደርግም ነበር » አሏት እሷንም ራሷቸውንም ለማሳመን ።

« እኔኮ አክስቴን አላውቃቸውም ። አባዬም ስለሳቸው ካለዚያ ቀን በስተቀር ሲናገር ሰምቼ አላውቅም » ስትል ዓይኖችዋ የእንባ ደመና እየጋረዳቸው ፣ ሳግ ንግግሯን እያሻከረው ውስጣዊ ፍርሃቷን ተነፈሰች ።

ወ/ሮ በላይነሽ ሰውነታቸውን ወደ ሕሊና አስጠግተው ፣ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከቱ ፤ በእጃቸው የሕሊናን እራስ እየደባበሱ « አይዞሽ መቼም ከዛ ከድህነት ኑሮ የማይሻል ነገር የለም። እንደሰማሁት አክስትሽ የታወቁ ሀብታም ናቸው ። ምንም ቢሆን ስጋቸው ነሽ አይዞሽ ጥለው አይጥሉሽም » አሏት ። ለማፅናናትና ለማረሳሳት ያህል ። ሕሊና አንገቷን አቀረቀረች ። « ምን መሆንሽ ነው ሕሊና ? መንገድ ሲሄዱ እየሳቁ እንጂ አይለቀስም ። ደግም አይደል ! » አሏት ። ወደደረታቸው ለማስጠጋት እየሞከሩ ።

« ድንገት ምን ሆና ነው ? » አሳቸው ከጎናቸው የነበረው ወጣት ። ወጣቱ ሁኔታቸውን ይከታተል ስለነበር ስሜቱ ሳይነካ አልቀረም ።

« ምን ትሆናለች ብለህ ነው ፤ እንደው ዝም ብላ ነው » ሲሉ መለሱለት ባጭሩ ። ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈለጉም ። ወጣቱ የተሰጠው መልስና የሚያየው ሁኔታ ሊጣጣሙለት አልቻሉም ። ውስጡን የሆነ የሀዘን ስሜት ጨምድዶታል ። የሕሊና ለቅሶ የእህቱን ያህል የሆነበት መሰለው ። የሴትየዋን ፊት ለማየት ጓጓ ።

« አመማት እንዴ ? » ሲል ጠየቃቸው ።

ወ/ሮ በላይነሽ ወጣቱን ልጅ ለአንድ አፍታ መልከት አደረጉ። ፊቱ ላይ መጥፎ ስሜት አይታይም ። « ልጂ ሀዘን ደርሶባት ነው » ሲሉ መልሳቸውን አሳጠሩ ።

ለወጣቱ ከመልሳቸው ይልቅ ገፅታቸውን ማየት መቻሉ እጅግ በጣም አስደነገጠው ። እራሱን እስኪጠራጠር ሁኔታው ተምታታበት።

« እማማ ከዚህ በፊት የማውቅዎት መሰለኝ . . . » አላቸው። ራሱን ለማረጋገት ፣ ሁኔታውን ለማጥናት ጊዜ ለማግኘት በማሰብ ።

ወ/ሮ በላይነሽ ወደ ወጣቱ ፊታቸውን መልሰው « እረ . . . ልጂ ምን ይታወቃል . . . በየቦታው ተቀጥሬ ስለሰራ ተገናኝተን



ይሆን? ለመሆኑ የት ነው ኑሮህ ? » በማለት ፈገግ ብለው ጠየቁት። አጋጣሚው ድንገተኛ ቢሆንም እራሱን አረጋጋ ። ወላጅ እናቱ በልጅነቱ ስለመሞታቸው እርግጠኛ መሆኑን ቢያውቅም የሴትየዋ ሁኔታ በብዙ መልኩ ከእናቱ ጋር መመሳሰል አስገረመው ። እናቱ አለመሆናቸውን ቢረዳም ሊለያቸው አልወደደም ። አብሯቸው ቆይቶ ቢያጫውታቸው ፣ ቢረዳቸው ተመኘ ።

« ኑሮዬ እንኳ ወደ አፍንጮ በር ነው ። እማማ . . . ደፈረኝ ባይሉኝ ፊትዎን ላይ እናቴን አስታወሱኝ ፣ ቁርጥ እናቴን ይመስላሉ . . . ድንገት ዝምድና ይኖራችሁ ይሆን ? »

ሕሊና የወጣቱ ንግግር የነበራትን ስሜት ነጠቃት ። አውቶቡስ ውስጥ ስትሳፈር ከመውደቅ የታደጋት ፣ አብሯቸው መቀመጡ ፣ . . . ሁሉ የሆነ ነገር ሳይኖረው እንደማይቀር አስላሰለች።

« የእኔ ዘመዶች ወሎየዎች ናቸው ። የሞቱት ሞተው የተረፉትም አሉ ። እኔ እንኳን ከሀገሬ ከወጣሁ ቆይቻለሁ ። የኖርኩት ግን መርካቶ መሀል ነው » አሉት ።

« እንግዲህ ሊሆን ይችላል » አለና በሀፍረት ስሜት ዝም አለ።

« ለመሆኑ ! እናትህ በህይወት አሉ ? » ሲሉ ጠየቁት ወይዘሮ በላይነሽ ።

ለወጣቱ መጥፎ ጥያቄ ነበር ። በቋፍ የነበረ የሀዘን ስሜቱ ተቀሰቀሰ ፣ እንደበቱ በሳግ ተወጥሮ እንባ ተናነቀው ። መንፈሱ ተረበሸ ። አንገቱን በቅሬታ ደፋ አድርጎ « ከሞተች ቆይታለች » አላቸው ።

« ተው እንጂ ልጂ ፣ ወንድ ልጅ እኮ አይሳሳም ። በዚያ ላይ እኔም እናት እሆንሃለሁ » አሉት ለማፅናናት ያህል ።

አውቶቡሱ አቃቂ ደርሶ የታፈነ በሩ እንደተከፈተ ተሳፋሪዎቹ እርስ በእርሳቸው እየተጋፉ ወረዱ ። ወ/ሮ በላይነሽን ከጎናቸው ተቀምጦ ሲያጫውታቸው የነበረው ወጣት በቦታው አልነበረም ። እንደድንገት ጥሏቸው መውጣቱ ፣ አካባቢ ያመላክተኛል የሚል ተስፋ ስለነበራቸው ተደናገጡ ። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነው ፣ የሕሊናን ከረጢት ከሥር ጎትተው ፣ ሕሊናን አስከትለው ከመውረዳቸው ወጣቱ ይጠብቃቸው እንደነበረ አወቁ ።

« እኔስ ጥለሽን የሄድኩ መስሎኝ ነበር ። እግዜአብሄር ይባርክህ ልጄ፣ እንዲያው ከዚህ ሀገር ሰው ብጠይቅህ ታውቃለህ ? » ሲሉ ጠየቁት ።

« እኔ እንኳን ለቦታው አዲስ ነኝ ። ለመሆኑ ማን ይባላሉ ?» አላቸው ።

« እዚህ ሀገር የታወቀ ቡና ቤት ያላቸው ሴት ናቸው ። ወ/ሮ አባይነሽ ይባላሉ » አሉት ። አላወቃቸውም ። የአካባቢውን ሰው መጠየቅ ነበረበት ። አንድ በእሱ ዕድሜ ያለ ልጅ አስቆመ ።

« የኔ ወንድም ! እባክህ ወ/ሮ . . . ማን ነበር ያሉኝ ? » አላቸው ወይዘሮ በላይነሽን ሥሙ ጠፍቶበት ።

« አባይነሽ ቡና ቤት » የት አካባቢ ነው የሚገኘው ? » ሲሉ የጀመረውን በመጨረስ ጠየቁ ።

« እንዲህ የሚባል ቡናቤት አላውቅም ። ለማንኛውም ቡና ቤት እዚህ አካባቢ የለም ። ትንሽ ወረድ ብላችሁ ብትጠይቁ ይሻላል» አለና መንገዱን ቀጠለ ። ወጣቱ ዕቃቸውን ተሸክሞ ፊት ፊት ወ/ሮ በላይነሽን እና ሕሊናን እየመራ ከአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ወጣ ብሎ ከሚገኘው ጋራ መሳይ ጉብታ ተነስተው ወደ ከተማው ወሰዳቸው ። በዝምታ እየተጓዙ ሳለ ፣

« እንዲህ ያለ የተባረከ ልጅ በአሁኑ ጊዜ ! . . . ልጄ ሥምህ ማን ይባላል ? » አሉት ዝምታውን በማባረር ።



« ሥሜ ያሬድ ይባላል . . . ያሬድ እንደሻው ። . . . የመባረኩን ነገር ግን ይርሱት » አላቸው ።

« ምነዋ ? . . . በዚህ ዕድሜህ ? እንዲህማ መሆን የለብህም። አይዞህ ሁሉም ያልፋል ። በዚህ ደግነትህ ለአንተ እንጀራ ያልወጣ ለማን ይወጣል ? ለመሆኑ ስንተኛ ደርሰሃል ? »

« መማር ምን ፋይዳ ይፈጥራል ብለው ነው እማማ ። ለነገሩ የሁለተኛ ዓመት ኮሌጅ ጨርሻለሁ ። አሁን ግን ትምህርቴን አቋርጬ ሥራ እየፈለኩ ነው ። ረዳት በማጣቴ ትምህርቴን ለመቀጠል አልቻልኩም ። » ወጣቱ ያሬድም ወ/ሮ በላይነሽን ፣

« ምን ሞቶባችሁ ነው ? እኔ እኮ መጀመሪያ ሳያችሁ እናትና ልጅ መሰላችሁኝ ነበር ። ለመሆኑ ምንዎ ናት ? » ሲል ጠየቃቸው።

ወ/ሮ በላይነሽ ችግራቸው የሚቃለልላቸው ይመስል አጋጣሚው ሲያመች ለጠየቃቸው ሁሉ ማስረዳት ይወዳሉ ። በዚያ ላይ ከልጁ ጋር የነበራቸው መቀራረብ ምን ይሉኝ የሚያሰኝ አልነበረም ። የራሳቸውን የኑሮ ሁኔታ ባጭሩ በመግለጽ ስለ ሕሊና የደረሰባትን ሀዘንና አሁን የት እንደሚሄዱ ታሪኩን አወጉት ። በመጨረሻም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ « የባሰ አታምጣ » ማለት ነው አሉና ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ከዚህ በኋላ አንዳችም ቃል ሳይለዋወጡ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ደረሱ ። ያሬድ ወደ ፋብሪካው በር እየተመለከተ « እማማ ፣ እዚህ መሥሪያ ቤት ስራ ለመቀጠር ዛሬ የፈተና ቀጠሮ አለኝ ። እንደው ቢቀናኝ ፣ እማማ እባክዎ በዚህ ንጹህ የድሃ አንደበትዎ ይጸልዩልኝ » በማለት ሠፍኖ የነበረውን ዝምታ ለመስወጥ ሞከረ ።

ወ/ሮ በላይነሽም ፀሎቱን ውለታ የመመለስ ያህል አድርገው ነበር የቆጠሩት ። እጃቸውን ወደ ሠማይ ዘርግተው « ልጄ ፣ ወዳጄ ቀንና ለሊት እፀልይልሃለሁ ፤ እግዚአብሄር ይርዳህ » ሲሉ ክልባቸው

ፀሎት አደረሱለት ። ቀጥለውም ተሸክሞላቸው የነበረውን ዕቃ ለመቀበል እጃቸውን ዘረጉ ።

« ጊዜው ገና ስለሆነ እስከ ከተማው እሸኛችኋለሁ » አለ ።

« አይ ግድየለ ! ግድየለ ተጋግዘን እናደርሰዋለን » አሉ ይሉኝታ ተሰምቷቸው ። ያ ባይሆን እንዲለያቸው አልፈለጉም ነበር። ለነሱ ከዚህ በኋላ ያለው የአድራሻ ፍለጋ የበለጠ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ተገንዝበውታል ። ያሬድም ከእናቱ አምሳያና ከምስኪኗ ሕሊና ተለይቶ መቅረቱን አልፈለገም ነበር ። የቀጠሮውን ሰዓት አለመድረሱን ምክንያት አድርጎ አብሯቸው መሄዱን ፈልጓል ። ዕቃውን እንደያዘላቸው አብረው ወደ ከተማው መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ፋብሪካዎች እንደብዛታቸው የአየር መበከልን አልፈጠሩም ፤ የዛፎችና የዕፅዋት መኖር የአቃቂን ከተማ ሰብአዊ ህይወት እስትንፋስ ሲጋት ላይ የሚጥለው አይመስልም ። ከጋሪ ፈረሶች የሚወጣው እዳሪ ብናኝ ግን አየሩን ብቻ ሳይሆን ሰውንም ጤና ነስቶታል ። ጥርጊያ መንገዶቹ ከዋናው መንገድ አንፃር ሲታዩ የእንግዳን ዓይን ይስባሉ ። የፋብሪካዎቹ መናኸሪያ የሆነችው ከተማ ከዋናው መንገዷ ዳርና ዳር ጥቅጥቅ ብለው ከተሰሩት ቤቶች የሽቀጣሽቀጥ ሱቆች ፤ የሕዝብ መዝናኛ ቡና ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ይገኛሉ ።

ለአቃቂ ከተማ ትልቁ መዝናኛ በመሆን የሚታወቀው የሾፌሮች ቡና ቤት በዚህ ዋና መንገድ ላይ ይገኛል ። በጉዞ ላይ እንዳሉ ወ/ሮ በላይነሽ ለብቻ ገንጠል ብለው ወደ አንድ ቤንዚን ማደያ ታጠፉ ። የማደያው ሠራተኛ ሁኔታቸው የልመና ስለመሰለው በጥላቻ ገላምጦአቸው ስራውን ቀጠለ ።

« ምን ትፈልጊያለሽ ? ናፍታ አሁን አይሸጥም ! ከዚህ ዞር በይ! » ሲል ጮኸባቸው ፤ የማደያው ሰራተኛ በተሰላቸ ስሜት ።



« እባክህ የኔ ወንድም ናፍታ ለመግዛት አይደለም የመጣሁት። የሰው ቤት ለመጠየቅ ነው » አሉት የሰሙትን ያልሰሙ ያህል ሆነው።

ቤንዚን አዳዩ የሆነ ደረሰኞችን በትከሻው ወደአንጠለጠለው ቦርሳ እየከተተ በለለቸና በችኮላ ቃል « ምን ዓይነት ሰው ነው ? እኔን ሕዝብ ግንኙነት ነው አሉሽ ? በይ ተናገሪ . . .ማን ይባላል ? » አለ ወደማደያው ቢሮ እየገባ ። ከኋላ ኋላው እየተከተሉ « የወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤት ። . . . እዚህ ሀገር የታወቀ ነው ። የቱ ጋ ይሆን?» አሉ በተደነባበረ አጠያየቅ ።

ቤንዚን አዳዩ አንገቱን ቀና አድርጎ ወ/ሮ በላይነሽን ከእግር እስከራሳቸው እየገላመጠ « ቡና ቤት » ሲል እራሱን ጠየቀ « አይ ሄ-ሄ-ሄ ! አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል አቃቂ እስከአሁን አልተወለደም። ይልቁንም ሥራ ባትፈቺ ይሻልሻል ። ኋላ መኪና እንዳይገጭሽ ከዚህ ዞር በይ ! » ሲል በንቀትና በማሾፍ ገላመጣቸው ።

በሁኔታው ግራ የተጋቡት ወ/ሮ በላይነሽ በሰውየው ንግግር ሳይሆን የተባለውን ቤት የሚያውቅ በማጣታቸው ግራ ተጋቡ ። አንገታቸውን በሀዘን አቀርቅረው አጋጣሚውን አማረሩ ። « ምነው ! እቶ የፊላ ሲዋሸኝ ነው እንዴ ? ተረት ይሆን እንዴ? ወ/ሮ አባነይሽ ቡና ቤት የሚባል አቃቂ የለም አለኝ ። ለምን ይሆን ? ወይስ ጆሮዬ ነው ? አንገታቸውን ደፍተው ወደ ያሬድና ሕሊና አመሩ ።

ያሬድ ከፊታቸው ላይ የነበረውን ሁኔታ አስተውሎ ቀድሞ « ምነው አልቀናዎትም እንዴ ? » ሲል ጠየቃቸው ።

ጥቂት ካመነቱ በኋላ « አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል አቃቂ የለም አለኝ፤ ባያውቀው ይሆናል » አሉ ።

መሀል ከተማ ደረሱ ። መንገድ ዳር ካለ ከአንድ ቤት ግድግዳ ሥር ወንበራቸውን ደርድረው ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱ ጫማ ጠራጊዎችን ጠየቁ ። ሁሉም እየተቀባበሉ አለማወቃቸውን ገለጹ ።

ያሬድ አንደኛውን ጫማ ጠራጊ « እስቲ ና ! » ሲል ተጣራ:: ጥሪውን ያዳመጠ ጫማ ጠራጊ ሮጦ የሊስትሮ ዕቃውን መሬት ላይ አስቀመጠ :: ያሬድ አንገቱን ቀና አድርጎ አስተዋለው ::

« ስማ አባይነሽ ቡና ቤት የሚባለውን ታውቃለህ ? » ሲል ጠየቀው ::

ለመጥረግ የነበረው ጉጉት እየከሰመ ከተቀመጠበት ቦታ ቀስ ብሎ ብድግ አለና በሀሳቡ እያወጣና እያወረደ ትንሽ ካመነታ በኋላ አንገቱን በአሉታ እየነቀነቀ « አባይነሽ ቡና ቤት ? የሚባል የለም » ሲል ተነፈሰ :: ቀጥሎም አጠገቡ ሜዳ ላይ የተቀመጡትን ጓደኞቹን በቋንቋው ጠርቶ አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል ያውቁ እንደሆነ ጠየቃቸው :: ሁሉም እርስ በርሳቸው በሹክሹክታ ተነጋግረው የደረሱበት መልስ ዝምታ ብቻ ሆነ ::

ጫማ ጠራጊው ያሰበው ግቡን ስላልመታ በስጨት ብሎ መሬት ላይ ያስቀመጠውን መሳሪያውን አንስቶ ወደ ጓደኞቹ ተቀላቀለ::

ያሬድ ግራ በመጋባትና ድንገት ተሳስተው እንደሆነ በማለት በመጠራጠር « ቡና ቤቱ እዚህ አቃቂ በለቃ ስለመሆኑ እርግጠኞች ናችሁ » ሲል ጠየቃቸው :: « እንግዲህ አቃቂ መባሉን ደጋግሜ ሰምቻለሁ » ስትል ሕሊና ተስፋ በመቁረጥ ተናገረች ::

« ድንገት ለቀው ወደ ሌላ ሀገር ሄደው ይሆን ? እንግዲህ በከተማው አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል ከሌለ ! . . . . » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ አፋቸው ላይ እንደመጣ ::

« አሁን ያ ደህ ሰው ቡና ቤት ያላት ዘመድ ብትኖረው ኖሮ ለምን ተጠግቶ አይኖርም ነበር? እኔም ሞኝ ነኝ :: በጣር ራሱን የሳተ ሰው ብዙ ያልማል . . . ህልሙን እውነት አድርጌ ይህችን ከርታታ በአጉል ተስፋ ማባዘኔ » ሲሉ በሃሳባቸው አብሰለሰሉ ::



እስቲ ደግሞ እዚህ ቡና ቤት ልግባና ልጠይቅ :: በይበልጥ የቡና ቤት ሠራተኞች ሊያውቁ ይችላሉ » ብሎ የያዘውን ዕቃ ለሕሊና ሰጥቶ ፈጠን ባለ እርምጃ ወደ ቡና ቤቱ አመራ :: ቡና ቤት እንደገባ ከፊት ለፊት አንድ ብቸኛ ወንበር ላይ የተቀመጠች ረዘም ያለች መልከመልካም ሴት ልጅ ጋ ጠጋ አለ ::

« ይቅርታ እህት ሰው ለመጠየቅ ነበር :: . . . ወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል ታውቂ እንደሆነ ብትረጂኝ ? » ሲል ጠየቃት ::

አስተናጋጅዋ ትኩር ብላ ተመለከተችው « አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል የለም :: ነገር ግን ወ/ሮ አባይነሽ የሚባሉ ቡና ቤት ያላቸው አውቃለሁ » አለችው :: ያሬድ በደስታ ተሞላ :: ልቡ ውስጡ ዘለለች:: የሆነ ሲቃ ያዘው :: « ሊሆን ይችላል :: ለነገሩ የምፈልገው ፅሁፉን ሳይሆን የቡና ቤቷን ባለቤት ነው :: የምታውቂ ከሆነ ባለውለታዬ ትሆኚያለሽ » አላት በጉጉት ውጪ ውጪውን እያየ :: ለንሕሊና ለመናገር ተጣድፏል ::

ልጅቱ አትኩራ ያሬድን እየተመለከተች « ለመሆኑ ለምን ትፈልጋቸዋለህ ? » የጥርጣሬ ሁኔታ ከፊቷ ይነበባል ::

ያሬድ አንገቱን ወደ ጎን ደፋ አድርጎ ፣ ገና መውጣት የጀመረ ፂሙን እየዳሰሰ በፈገግታ ልጅቷን እየተመለከተ « ከገጠር የመጡ ዘመዶቻቸው ስለሚፈልጓቸው ነው » አላት ::

« የትኞቹ ናቸው ? » አለች :: ያሬድ ጥያቄዋን ለመመለስ ወደ በሩ ሲሄድ ከኋላ ተከተለችው :: በሩ ላይ ቆም ብሎ ራቅ ብለው የቆሙትን ወ/ሮ በላይነሽንና ሕሊናን አመለከታት :: ልጅቷ ያየችውን እንዳመነች ሁሉ ፈገግ ብላ ያሬድን ከላይ እስከታች እየተመለከተች « እኔ እንደነገርኩህ እንዳትነግራቸው ዋ ! » አመልካች ጣቷን በማስጠንቀቂያ መልክ ካሳየችው በኋላ « ቡና ቤቱ ሾፌሮች ነው የሚባለው ያውልህ ! ከዛ ከግንብ ቤት አጠገብ ያለው ቢጫ ቀለም የተቀባው ነው » አለችው ::

ተያይዘው አልቤርጎውን በትይዩ ታከው በመኖሪያ ቤቱ ጠርዝ በኩል በጓሮ በር ወደ ውስጥ ገቡ ።

« እዚህ ተቀመጡ » በማለት ወፍራሟ ሴት በዕቃና በጠርሙስ የተጨናነቀ ክፍል ውስጥ መቀመጫ ወደ አለበት እያመለከተች እረፍ እንዲሉ ጋበዘቻቸው ። ሕሊና በጣም ተዳክማለች:: ካፊያው በላያቸው ላይ ነበር ያለቀው ። በቤቱ ውስጥ የተዳፈነው የእልክል ሽታ ሕሊናን አልተስማማትም ።

ሴትዬዋ « ምን ይምጣላችሁ ? ቡና ወይስ ሻይ ? » ስትል ወ/ሮ በላይነሽንና ሕሊናን ጠየቀች ። ሕሊና ሻይ ፣ ወ/ሮ በላይነሽ ደግሞ ቡና እንደሚሻላቸው ተናገሩ ። በሩ ላይ ቆሞ ሲያዳምጥ ለነበረው ዘበኛ « ፈሩቅ ሁለት ቡናና አንድ ሻይ ይዘህልን ና ለማርታ እስካበች ናት ያለችው በላት ። » ትዕዛዝ ሰጥታ የሕሊናን ዓይን ዓይን መመልከት ጀመረች ።

ሁሉም በዝምታ ተፋጠው የቀረበውን ሻይና ቡና ጠጥተው እንደጨረሱ በመካከል ከውጭ የመኪና ጡሩምባ ድምጽ ተሰማ ። እስካበች ከመቀመጫዋ ብድግ ብላ « እትዬ መጡ ፤ በሉ እንግዲህ . . . » በማለት የጀመሩትን ሳይጨርሱ በፍጥነት ከክፍሉ ወጣች ።

ወ/ሮ በላይነሽና ሕሊና ፊታቸው ላይ የመሸበርና የፍርሃት መልክ ቢታይባቸውም « አይዞሽ እንግዲህ ደርሰሻል ። የምታይው ሀብት ሁሉ እንኳን ለአንቺ ቀርቶ ለባዕድም ይተርፋል » ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ ሕሊናን አፅናኗት ። ሕሊና ግን ፣ የምታየውና የምትገምተው ሀብት ሁሉ አላማራትም ። ያው የነበረችበት የድህነት ኑሮዋ ይሞቃት እንደነበር ተሰማት ። ሆድ ባሳት ። ዓይኖችዋ እንባ አዘነቡ ።

ወ/ሮ በላይነሽ « ምነው ነውርም አይደል ! በእንግድነት መጥቶ በደስታ ቤት ሀዘን ማምጣት ? በይ ዝም በይ ልጄ ! » ሲሉ ሊያበረታትዋት ሞከሩ ። በዚህ መካከል አንድ በጣም ወፍራም የሀበሻ



ቀሚስ የለበሱ ዘመናዊ ሴት በሩን ሞልተው እንደቆሙ ወደ ክፍሉ ውስጥ አማተሩ ። « ትንሽ ቆይተዋል ፤ ቤቱ ጠፍቷቸው በፍለጋ ነው ያገኙት » በማለት ስትፈራ ስትቸር እስካበች ከኋላቸው ሆና ተናገረች ።

ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ለሠላምታ ከተቀመጡበት ተነሱ ። ወ/ሮ አባይነሽ ሕሊናን ከእግር እስከ እራሷ አትኩረው እየቃኟት ወ/ሮ በላይነሽን « በግዜር ይቀመጡ ይቀመጡ » አሉና ፈሩቅ ወንበር እንዲያመጣላቸው አዘዙት ። ያዘዙት መቀመጫ እንደመጣ ከወ/ሮ በላይነሽ አጠገብ ተቀመጡ ። ያቺ ክፍል የዝምታ ጫና ወረደባት ።

እስካበች ዝምታው ስላልጣማት ፣ ሕሊናን እየተመለከተች « እትዬ ወርቂቱን አትመስልም ? እብሶ የፀጉሯ ነገር በጣም ይገርማል » አለች ።

« ወደ ሥራሽ ሂጂ ! ሥራ ፈት » አሏት ወ/ሮ አባይነሽ በቁጣ ። እስካበች ሹልክ ብላ ወጣች ። ሕሊና ውስጧ ተረበሸ ፤ ሰውነቷ ሲሸማቀቅ ታወቃት ። አክስቷ ኃይለኛና ቁጡ እንደሆኑ ፣ ለእሷ እንደማይመቹ ገመተች ። አባቷን አሰበች ።

« እንግዲህ ከመጣሽ ደህና ። ግን አባትሽ ጨከና እንዴት ጣከሽ ? » ሲሉ ወ/ሮ አባይነሽ የሕሊናን ከረጢት እየተመለከቱ ያልታሰበ ጥያቄ አቀረቡ ። « አይ-ይ ነገሩስ ወዲህ ነው ! » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ፊት የጎድን እያዩ ወዲያው እንባቸው ዓይናቸው ላይ አቀረረ ። ቀጥለውም ሲፈሩ ሲቸሩ የአባቷን ሞት በማሳዘን ለወ/ሮ አባይነሽ አረዷቸው ።

« ድሮውንም ብዬ ነበር ። ያቺ ከላባ እናቷ ከማይሆን ሰው ጋር ፍቅር ፍቅር ብላ እንደከበት ከደህና ቤቷ ስትኮበልል ፣ እስኪ ምን አሰኛት ? የምትበላው ፣ የምትጠጣው ሳታጣ » ። ሕሊና የአክስቷን ክፋት ቀደም ብላ ከአባቷ አነጋገር ስለተረዳች አልገረማትም:: አክስቷ በአባቷ ላይ ስለነበራቸው ጥላቻ አባቷ

« እትፍረጂባት » ብለው የነገሯት ትዝ አላት ፡፡ ግን ምንስ ቢሆን ከሥጋቸው ወልዷል ፡፡ ወ/ሮ አባይነሽ መርዶውን ሰምተው እንባ ያለማፍሰሳቸው ቢገድም ለይስሙላ አለማዘናቸው ለሕሊና እንቆቅልሽ ሆነባት ፡፡ ይህን የተገነዘቡት ወ/ሮ በላይነሽ ሁኔታውን ለማረጋጋት የአባቷን ኑሮ ፣ የሞተበትን ሁኔታ ከንፈር እየመጠጡ አስተዛዝነው ቢነግሩም ያሰቡት ሊሳካላቸው አልቻለም ፡፡

« እንግዲህ እሷም ልጃችን ናት ፣ እየመጣን እንጠይቃለን ፣ እሷም እየመጣች ትጠይቀን ፣ እኔም ይመሽብኛል ወደቤቴ ልግባ » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ፡፡

« በሉ እንግዲህ አባቷ ካሉት ሀብቶቹ እሷን ካወረሰኝ ስልጡን አርጌ አሳድጋታለሁ ፣ እሷም እንደእናቷ እስከምትከበልል ፡፡ ግን ከእንግዲህ ዘመድ አለኝ ብላ ወዲያ ወዲህ መሽከርከር የለባትም ፡፡ እናንተስ ምን በወጣችሁ በሰው ዲቃላ እዚህ ድረስ የምትለፉት ፡፡ እሷስ ከእንግዲህ ምን ይከፋታል ብለው ነው ? » በማሾፍ እየተናገሩ ከመቀመጫቸው ተነስተው ፈሩቅን ተጣሩ ፡፡ ፈሩቅ አፍታም አልቆየ፡፡ ትዕዛዝ ለመቀበል ከወ/ሮ አባይነሽ ፊት ከመቆሙ ፣

« በል እንግዲህ እሳቸው እ - ወ/ሮ . . . »

« በላይነሽ » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ እራሳቸውን በማስተዋወቅ ዓይነት ፡፡

« አዎ ወ/ሮ በላይነሽን ሸኛቸው ፣ በዛውም እስካበችን ጥራልኝ » አሉት ፡፡

ወ/ሮ በላይነሽ በሀዘንና በማጽናናት ዓይን ሕሊናን እየተመለከቱ ከመቀመጫቸው ተነስተው ወደ በሩ ሊወጡ ሲጠጉ ሳያስቡት ከኋላቸው ሕሊና አንገታቸው ላይ ተጠምጥማ እየተንሰቀሰቀች አለቀሰች ፡፡ የእንባዋ አፈሳሰስ እስከወዲያኛው ይመስል ነበር ፡፡ ወ/ሮ በላይነሽ ዞር ብለው ሕሊናን በጉያቸው አቅፈው አይዞሽ ! አይዞሽ እያሉ ለማጽናናት ሲሞክሩ ከቁጥጥራቸው



ውጭ በሆነ ሁኔታ እንባቸው እርግፍ እርግፍ ሲል ለስለስ ያለ ድምፃቸውን አሰሙ ፡፡

« ምነዋ እቴ ! በቤቴ ጉሪ ፊቻ ባትሉብኝ ፣ አታልቅሱብኝ ! ምነው እርሶ ደግሞ ትልቅ ሰው አይደሉም እንዴ ? » ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ ላይ ጮኹባቸው ፡፡

« እመይቴ ! እመይቴ ! በህይወቴ እንደዚህች ልጅ የምወደውን ማህፀኔ ለማፍራት አልታደለም ፡፡ ልጄ እኮ ነች ልጄ ! ልጄ ! በማልቀሳችን አይፍረዱብን » ሲሉ ተማፀኗቸው ፡፡

* * *

ቀጠሮው ቦታ ቀድሞ የደረሰው ሀሰን ነበር ፡፡ ከቤቱ ሲወጣ የሆነ ነገር እየተጫጫነው ፣ እየቀፈፈው ቢሆንም የጓደኛው ማርፈድ ደግሞ ብሽቀቱን ጨመረበት ፡፡

« አይሞላልህ ! ዛሬ ደግሞ ምን አጋጠመኝ ልትል ይሆን ይህን ያህል ያረፈድከው ? » ሲል ፀጋው ላይ በቁጣ ጮኸበት ፡፡

« አንተ የደላህ ነህ ወንድሜ ፣ . . . ይልቅስ ሰዓት እንዳያልፍብን እንፍጠን » አለና ወደፊት ተራመደ ፀጋው ፡፡ ቃል ሳይለዋወጡ የሚፈልጉበት የአውቶቡስ ፌርማታ ደረሱ ፡፡

« እመቤት ዘጠኝ ቁጥር አውቶቡስ አልፋለች ? » ሲል ፀጋው ከፌርማታው የነበረች መልከመልካም ወጣት ጠየቀ ፡፡

« ከመጣሁ አላየኋትም » ስትል ባጭሩ መለሰችለት ፡፡

ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም ፡፡ ፌርማታው ውስጥ የሆነ ጥግ ቦታ ፈልገው ተቀመጡ ፡፡ « እንዲያው ለነገሩ እንጂው ብለን ካልሆነ እስከአሁን ዘመድ ሳይከቱበት ቀረ ብለህ ነው ? » አለ ሀሰን ፡፡

« አንተ ደግሞ አንድ ነገር ሳትጀምር ለመጨረስ ትሮጣለህ !» አለው በቁጣ ፡፡

« በአስከዛሬው ድካማችን . . . » ዝም አለ ሀሰን ::

በመካከል ይጠብቁት የነበረው አውቶብስ መጣና እየተጣደፉ ተሳፈሩ :: ከተሳፋሪው ጋር ተቀላቅለው ጉዞአቸውን ቀጠሉ :: አውቶቡሱ በየፌርማታው እያቆመ ገቢና ወጪውን ሲያስተናግድ ከቆየ በኋላ እንደ ድንገት ያልጠበቁት ጩኸት ተሰማ :: አውቶብሱም እንደስካራም ወዲያና ወዲህ ተንገጫግጮ የሚዘገንን ድምፅ በማሰማት ቀጥ አለ :: ተሳፋሪው እርስ በእርሱ እየተያየ አጉረመረመ :: ኡኡታ ተሰማ :: ሁሉም ኡኡታው ወደመጣበት አቅጣጫ አስተዋለ :: እነ ፀጋው በአሉበት አካባቢ አንድ በመሀከለኛ ዕድሜ የሚገኝ ጋቢ የለበሰ አጠር ያለ ሰውና የለበሰውን ኮት ግማሽ ድረስ በማውለቅ ደረቱን ገልብጦ የሚቀልድ ከሚመስል ሰው ጋር ይጨቃጨቃሉ :: ጋቢ የለበሰው ጀንበሬ ደርብ ይባላል ::

የደብረታቦሩ ልጅ ይገፍሃለሁ ! መልሳት ! አለቅህም ዛሬ ደምህ ከደሜ ! » እያለ ጀንበሬ ይጮሀል :: ኮት የለበሰው የተሳፋሪውን ዓይን ለመሳብ እየሞከረ « ምን አድርግ ነው የሚለኝ ፤ እባካችሁ አላቁኝ :: እብድ ነው እንዴ ? » አለ ስቆ ለማሳቅም ፈገግ ብሎ :: ሁኔታቸው ገብቶት የነበረው ሹፌር ዞሮ መጥቶ እጁን ወደኮት ለባሹ እየጠቆመ « መልሳት ! መልሳት ነው የምልህ » አለው ::

« ያልወሰድኩትን ከየት አመጣለሁ » ሲል በሹፌሩ ላይ ተሳለቀ:: ሾፌሩም በእልህና በንዴት ኮት የለበሰውን አንድ በአንድ ኪሱን ይፈትሸው ጀመር :: ምንም ነገር ሊያገኝ አልቻለም ፤ ከአንድ አንድ ብጣሽ ወረቀትና የተለያዩ ጨርቃ ጨርቆች በስተቀር :: ሾፌሩ ፍተሻውን እንደጨረሰ ጋቢ ለባሹን መለስ ብሎ እያየ « ቀደም ብለው ጥለውት ይሆናል :: እንደአየሁት ይህ ሰው ገንዘብዎን አልወሰደም » አለና በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ተመለከተ :: በዚያው ሁኔታ ጋቢ ለባሹ የሹፌሩን ዓይኖች ተከትሎ ዙሪያውን በአጠሩት ሰዎች ላይ



ዓይኖቹ ተንቀሳቀሱ :: ድንገት ዓይኖቹ ሀሰን እና ፀጋው ላይ ሲደርሱ እይታቸው ተገታ ::

« ብሬን ! ሰዎች ጉድ ሆንኩ እኮ ! ተዘረፍኩ :: » ብሎ ሀሰንን እና ፀጋውን ልብሳቸውን ጨምድዶ ያዛቸው :: « ብሬን መልሱልኝ » በማለት እሪታውን አቀለጠው :: »

* * *

ጠረጴዛ ላይ ተቀመጦ ፊት ለፊቱ የነበሩትን ሁለት ሰዎች በማነጋገር ላይ ያለ የደንብ ልብስ የለበሰ ፖሊስ ካለበት ክፍል ጋቢ ለባሹ ፤ ፀጋውና ሀሰን በፖሊስ ታጅበው ገቡ :: አጃቢው ፖሊስ ወታደራዊ ሠላምታ ከሰጠ በኋላ « እነኚህ ሁለት ወጣቶች ከዚህኛው ሰው ሁለት መቶ ብር ሰርቀዋል ስለተባለ አምጥቻቸዋለሁ» ሲል ወደዝርዝሩ ሳይገባ በአጭሩ ተናገረ :: ከዚያም አስረክቦ ወጣ :: ለሰቃው ቀደም ሲል አብረውት የነበሩትን ሁለት ባለጉዳዮች « በኋላ እንቀጥላለን » ብሎ ውጭ እንዲቆዩ አሰናብቶ ፊቱን ወደ እንግዶቹ መለሰ ::

« እንዴት ነበር ዘረፋው » አለው ባለ ጋቢውን ::

ፀጋው ቀደም ብሎ ሁኔታውን ለማስረዳት ሲሞክር ፖሊሱ « አንተን የጠየቀሀ የለም ፤ ዝም በል » ሲል ገሰፀው :: « ጌታዬ ቢፈተሹ አሁንም የዘረፉት ሁለት መቶ ብሬ በእጃቸው ይገኛል » ሲል ጋቢ የለበሰው ወደ ሀሰን እጁን በመጠቆም እንዲፈተሹለት ተማፀነ ::

« ታዲያ ለምን አትመልሱም ? ሲነቃባችሁም አታውቁም ?» አላቸው ፖሊሱ ጎርነን ባለ ድምፅ እነ ፀጋውን ከአንዱ ወደ ሌላው እየተመለከተ ::

ፀጋው ለመናገር በጉጉት ዕድል ሲጠብቅ ነበረና አጋጣሚውን ተጠቀመበት :: « ጋሼ እኛ አልሰረቅንም :: ሰውየው ከኛ በፊት ሌላ

ሰው ሰርቆብኛል ብሎ አውቶቡሱ ውስጥ ሲጮህ ነበር ። እኛ ስንወርድ ምን እንዳሰበ አናውቅም እኛን ሰርቃችሁኛል ብሎ አስያዘን ? » በማለት በማሳዘን ስሜት ለማስረዳት ጣረ ።

« ለመሆኑ ስራችሁ ምንድነው ? » ሲል ጠየቃቸው ፖሊሱ።

« ለጊዜው ሥራ የለንም ። በዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ነበርን ። ዛሬ ሥራ ለመቀጠር የፈተና ቀጠሮ ስለነበረን ወደ አቃቂ ለመሄድ ስንል ነው ይህ ጉድ የገጠመን » ሲል ሀሰን መለሰለት ።

« የተሰረቀብህ ዝርዝር ብር ነው ጥቅል ? » ሲል ፖሊሱ ባለጋቢውን ጠየቀው ።

« ሚስቴን ሆስፒታል አስገብቼ ለድንገተኛ ከሀገሬ ከደብረታቦር ያመጣሁት አራት ባለ ሃምሳ ጥቅል ብር ነበር » አለ ።

ፖሊሱም ሀሰንን « ና ወደዚህ ቅረብ ። ኪስህ ውስጥ ያለውን ዕቃ እዚህ ላይ አስቀምጥ » ወደ ጠረጴዛው ጫፍ በጁ እያመለከተ አዘዘው ።

ሀሰን ከላይኛው ከኮት ኪሱ ጀምሮ ያሉትን ሁሉ እየፈተሸ በውስጣቸው የሸከፋትን ዕቃ እያወጣ አስቀመጠ ። ከኪሱ ሁለት ዝርዝር ብርና ሳንቲሞችን አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ ሲያስቀምጥ አንድ ስሙኒ ከእጁ አምልጦ ወለሉ ላይ ወደቀ ። ለማንሳት ጎንበስ ሲል ፖሊሱ « ግድ የለም ተወው » አለውና ወደ ባለጋቢው ዞሮ ፣

« ለመሆኑ ሥምህ ማን ይባላል ? » ሲል ጠየቀው ።

« ጀንበሬ ይባላል ጌታዬ ፤ጀንበሬ ደርብ » ሲል በማስተዛዘን ደጋግሞ መለሰለት ።

« በል አቶ ጀንበሬ የወደቀውን ሳንቲም አንስተህ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጥ » አለውና ፍተሻውን ቀጠለ ። በመጨረሻም « በል ሱሪህን ፍታ» ሲል ሀሰንን አዘዘው ። ሀሰን የታዘዘውን ፈጸመ ። ፖሊሱ ፀጋውንም ፈተሸ ። የተሰረቀው ገንዘብ ሲገኝ አልቻለም ።



ፀጋው ኪስ ውስጥ የተገኘው አንድ ባለ አምስት ብር ኖትና ሃያ ሳንቲም ብቻ ነበር ።

ፖሊሱ ጣቱን አፍንጫው ላይ አስሞርክዞ ትንሽ ከተከዘ በኋላ « ለመሆኑ ቀደም ሲል ሰረቀ የተባለው ሰው ምን ዓይነት ነው » ሲል ጠየቃቸው ።

« አጠር ያለ ፣ ጠይም ፣ አለባበሱ ዘመናዊ ፣ ፂም ያለውና ፊቱ ላይ ከግንባሩ ገደማ ጠባሳ ያለው ነው » ሲል ሀሰን ለመግለጽ ሞከረ ።

« የሰውየው አለባበስ ምን ይመስላል ? » ሲል በድጋሚ ጠየቀ ።

« በጣም ደህና ነው ። ከላይ እስከታች ሱፍ ነው የለበሰው ። ሠዓትና ትልቅ የወርቅ የጣት ቀለበት ያደረገም ይመስለኛል » በማለት ፀጋው መልስ ሰጠ ።

ፖሊሱ ሥዕላዊ መግለጫውን በአምንታ መልክ ራሱን እየነቀነቀ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ እነ ፀጋውን ዕቃቸውን እንዲወስዱ አዘዘ ።

ቀጥሎም « አቶ ጀንበሬ ሌባውን ለቀውታል ። ይህ የተባለው ሰው በዘጠኝ ቁጥር መስመር የታወቀ ሌባ ነው ። በሉ እናንተ ሥማችሁንና አድራሻችሁን ስጡና ወደ የስራችሁ ሂዱ » ሲል አሰናበታቸው ።

« በምንም ዓይነት ! ዘራፊዎቹን መልቀቅዎ ትክክል አይደለም ! ተዘርፌ ልቀር !» እያለ እጆቹን ራሱ ላይ አድርጎ « ጉድ ነው ! ጉድ ነው ! » ሲል ባለጋቢው ጀንበሬ ጮኸ ።

« አዳምጥ አቶ ጀንበሬ ! » አለው ፖሊሱ « እኛ ሰዎችን ከሜዳ ላይ ለብስበን ሌቦች ብለን አናስርም ። ሌቦች ያልካቸው ሰዎች ለሌብነታቸው ማስረጃ የሚሆን ምንም ተጨባጭ ነገር ስለአልተገኘ ባቸው ወንጀላቸው ግልጽ አይደለም ። ከፈለክ ሰርቀውኛል ስትል

« መስራት እችላለሁ ነው የምትይው ? እዚህ አካባቢ የሚሰራው ሥራ ምን ዓይነት እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ለአንቺ መናገሩም ይዘገንናል ። » አለቻት አስካበች በመራር ስሜት ።

« ከእንጨት መሸከም ፣ ከቤት ቤት እየዞሩ በግርድና ከመስራት የበለጠ ከባድ ሥራ የለም ። በጉልበቴ ሠርቼ ማደር ከአባቴ የወረስኩት መልካም ምግባር ነው ። » አለቻት ሒሊና በየዋህነት ። አስካበች እንድታወቅ የፈለገችው ነገር እንዳልገባት ተገነበበች ።

« በይ እንግዲህ ለማንኛውም ከረጢቱን ፍችና ዕቃሽን በመልክ በመልኩ አስቀምጭ ፣ ዐጉርሽንም ተጣጥበሽ የሚመጣውን ጠብቂ » አለቻት ።

ሒሊና የታዘዘችውን ለመፈፀም ከረጢቷን ፈትታ ከውስጥ ያለውን ዕቃ ማውጣት ጀመረች ። በመጀመሪያ ያረጁ የአባቷን ልብሶች አወጣች መጥረቢያ ተከተለ ። ሒሊና በልዩ ስሜት « የአባቴ መጥረቢያ » ብላ አፍንጫዋን እጀታው ላይ አሳረፈች ። አስካበች በሒሊና ባህሪ በመገረም እንደጉድ ታያት ጀመር ። ሒሊና የመጥረቢያውን እጀታ መሀሉ ላይ በሁለት እጆቿ ጥርቅም አድርጋ ደረቷ ላይ ለጥፋ እንባዋን ለቀቀችው ።

« የማናት ሞኝ እባካችሁ ። በይ አሁን መጥረቢያውን አልጋ ስር አስቀምጪውና ተንቀሳቀሽ » አለቻት አስካበች ፊት ላለመስጠት ያህል ለመቆጣት እየሞከረች ።

« የሞኝነት አይደለም ። አባቴ ያወረሰኝ ቢኖር ይህን መጥረቢያ ነው ። ይህ መጥረቢያ ሁልጊዜ አባቴን ከነደግነቱ፣ ከነሥራ ወዳድነቱ ያስታውሰኛል ። ብርታትም የሚሰጠኝ ይመስለኛል ። » ስትል ሒሊና ተናገረች ።



እንደድንገት የአስካበች ስሜት ተለዋወጠ ። በሒሊና ውስጥ የሒሊናን አባት ለማየት ሞከረች ። አባቷን ደግሞ ከሒሊና አባት ጋር አነፃፀረች ።

« የኔ አባት ብዙ ከብቶች ነበሩት ። ለመጀመሪያ ባሌ እስገድዶ ከዳረኝ በኋላ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ዞር ብሎ አይቶኝም አያውቅም ። ገና ሳላገባም አባቴ ወንድሞቼን እንጂ እኔን ከመጤፍ አይቆጥረኝም ነበር ። በዚህ የተነሳ አባቴን በፍቅር ተመልክቼው አላውቅም ። ሲሞትም መቃብሩ ላይ አልቆምኩም ። አባቴ ከመሞቱ በፊት ከተማ ይወድ ነበር ። ታዲያ ከእትዬ ጋር ወዳጅነት ተያይዘው ሳሉ ያለውን ሀብት ሙጥጥ አርጎ ሸጦ እሳቸው ቤት ገባ ። እኔም ኑሮው አልሆንልኝ ይልና ከባሌ ጋር ተጣልቼ ወደ ወላጆቼ ጋ ስሄድ አባቴ ዓይንሽን ላፈር ብሎ ወደዚህ አመጣኝ ። ታዲያ ይሄውልሽ ውሉ ባልታወቀ ወይ በቅጥር ወይ በዝምድና ልፈታው በማልችለው ሁኔታ እዚሁ ታስሬ ቀረሁ ። አሁንማ ምን ይደረጋል መሄጃውም ጠፋ ። » ሀሳቧን ገታ አድርጋ ፤ « ከዚህ ቤት ጋር ያቆራኘኝ አንዳች ነገር አለ ። መሄድ እየፈለኩ አልቻልኩም» ስትል ቀጠለች ። ከሒሊና አስተያየት ማግኘት አልቻለችም ።

« ሒሊና አሁን ያጫወትኩሽ ምስጢር ነው . . . እርቦሻል መሰል » ብላ መልስ ሳትጠብቅ ከበሩ ሥር ቁምሳጥን መሳይ ሳጠራ ላይ በጨርቅ ተከድኖ የተቀመጠውን ዝርግ ሳህን አቀረበችላት ። አልፎ አልፎ ሽሮ መሳይ ወጥ የነካካው እንጀራ ነበር ።

« በይ እንግዲህ ብይ ! የሚመጣው ነገር አይታወቅም » ።

በሚቀጥሉት ቀናት ሒሊና የቤቱን ነዋሪዎችና የስራውን ሂደት ተመለከተች ። በአክብሮትና በተራ ሥም የሚጠሩትን ለይታ አጠናች። ወ/ሮ አባይነሽን « እቴቴ » ስትላቸው ባይቀበሉትም ደፍረው « አትበይኝ » ማለት አልቻሉም ። አስካበችንም « እትዬ » ስትላት ሌሎችን እንደየዕድሜ ድርሻቸው ወንዶችና ሴቶችን በመለየት

ወደ ውስጥ ስትዘልቅ ሕሊና በመጠኑም ቢሆን ለመረጋጋት ሞከረች ::

ወ/ሮ አባይነሽ በቁጣ እንደተንጨረጨሩ የእንጨት ዘር ለማግኘት ሲማትሩ ዓይናቸው ግድግዳውን ታክ የተጋደመ መጥረቢያ ላይ አረፈ ::

« ይሄ ደግሞ ምናችሁ ነው ? » ሲሉ በመገረም ጠየቁ ::

« የልጅቱ ትራስ ነው » አለች አስካበች የሕሊናን ስሜት በመረዳቷ ::

ወ/ሮ አባይነሽ ወደ ሕሊና እየተመለከቱ « ገፊ ! ዘመዶችሽን ሁሉ አስናብተሽ እኔን ደግሞ ልትገፊ ነው የመጥረቢያ ትራስ የምታደርጊው ! በይ ባስቸኳይ አንሽው » ብለው ዞር ሲሉ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን በቅርቡ የተነሱትን ፎቶግራፍ ተመለከቱ :: በየቀኑ ከሚመለከቷቸው የቀድሞ ፎቶግራፎች ጋር አወዳደሩ :: በእስካበች ክፍል የተሰቀለውን ፎቶግራፍ ግን አልወደዱትም :: የቀድሞ ውበታቸውን አደብዝዞ እርጅናቸውን አጉልቶ ተስፋቸውን እመነመነው :: አላስቻላቸውም ::

« አስካበች እባክሽን ምን አደረኩሽ ? ይሄን ፎቶግራፍ ከፊቴ ብታነሽው ? ስንት ቀን ልንገርሽ ? » ብለው በፍጥነት እርምጃ ከክፍሉ ወጡ ::

አስካበች የወ/ሮ አባይነሽን ፎቶግራፍ አንስታ ከድንኩ አልጋ ሥር ካለ የእንጨት ሳጥን ውስጥ በልብሶቿ መሀል አስቀመጠችው :: ቀጥላ ትርጉሙን ለመለየት በማይቻል ድምፅ እያጉረመረመች ወደመጥረቢያው ተመለከተች :: ፊቷን ከመጥረቢያው ስታነሳ ከሕሊና ጋር ዓይን ለዓይን ተገናኙ ::

« ሕሊና እኚህ እርጉም ሴትዬ አይለቁሽም ልውሰድና ኩሽና ላስቀምጠው » አለቻት :: ሕሊና ውስጧ ተላወሰ :: የማታውቀው መጥፎ ስሜት ወረራት ::



« እትዬ በህይወቴ ያለኝ ቅሪትና ተስፋ እሱ ብቻ ነው :: » ስለች ቀይ ፊቷን በእጆቿ ሸፍና ጣራ ጣራውን እያየች ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ::

« እትዬ መጥረቢያውን ስጪኝና ከዚህ ቤት እጠፋለሁ » ስትል እጆቿን ወደ አስካበች ዘረጋች ::

አስካበች በልመናና በቅሬታ ዓይነት ፣ እንድም በማዘን ሌላም በፍርሃት ፣ « ሕሊና የእትዬን ፀባይ ያወቅሽው ይመስለኛል :: መጥረቢያው ከእሳቸው ህይወት ጋር የተገናኘ ስለመሰላቸው ፣ በመጥፎ ስሜት አይተውታል :: የትም ብትሄጂ አይለቁሽም :: ይልቅስ ኩሽና ወስጄ ላስቀምጠው » አለቻት ::

« ለእኔኮ የአባቴ ሽታ ነው » አለች ሕሊና ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች :: አስካበች ሆድዋ ሲጨክን አልቻለም :: ሕሊና አንጀቷን በላቸው ::

« በቃ ተይው :: ባይሆን ልብስሽ ውስጥ ደብቂው :: የሚሆነውን እናያለን » አለችና « በይ ዕንባሽን ጥረጊ ፤ እትዬ እንደሆኑ በላቸው ቤት ከፍቶት የሚያለቅስ ሁሉ ሟርተኛ ነው :: » ስትል ምክሯን ለገለቻት ::

ወ/ሮ አባይነሽ ፊታቸውን ኮሶ አስመስለው ፣ ጋቢያቸውን ደርበው መኝታ ክፍል ውስጥ ከተረኛው የወንድ እንግዳቸው ጋር ቢጠጡ አምሽተው እንኳ የቀኑ ንዴታቸውን በውስጣቸው አምቀዋት ነበር ::

« ሕሊና » ሲሉ ተጣሩ :: ሕሊና ድጋሚ አልተጠራችም ::

« አቤት » ብላ የመኝታ ቤቱን በር ከፍታ ገባች ::

« የእግር ውኃ እሙቀሻል ? » ሲሉ ጠየቋት :: መልሱን ሳይጠብቁ « ወንበር አምጪና የአብዬ ጋሻዬን ልብስ ተቀበይ » ሲሉ አዘዟት :: ከመብል ጠረጴዛ አጠገብ ከተደረደረው ወንበር አንዱን ብድግ አርጋ ወደ መኝታ ቤት ወሰደች :: አብዬ ጋሻዬ ልብሳቸውን

« ተቀብለውን ይሆን እንዴ ? እኔ መቼም አላምንም » አለ ሀሰን ::

« ምን አስቸኮለህ መጥተን የለ ! ለማንኛውም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተቀብለናል ወይም አልተቀበልንም ይሉናል » አለ ፀጋው እርምጃውን በማፋጠን ::

አስተዳደሩ ቢሮ አካባቢ ሌሎች በርካታ የፋብሪካ ሠራተኞች አስተዳደሩ ቢሮ ለመግባት ተራቸውን ይጠብቁ ነበር :: ወረፋ ጠብቆ የመግባቱ ነገር አስቸጋሪ መስሎ ታያቸው :: ሀሰን እነሱ የመጡበት ጉዳይ የተለየ መሆኑን በመግለጽ የተላላኪውን ትብብር መፈለጉ እንደሚሻል ሀሳብ አቀረበ :: ሁሉም ለውጤቱ ጓጉተው ስለነበር በሀሳቡ ተስማሙ :: የቆሙትን ባለተራዎች እያለፉ ወደ ተላላኪው ቀረቡ ::

« ይስሙ ጋሼ ባለፈው ሣምንት ለቅጥር ፈተና ወስደን ፣ ዛሬ እንድንመጣ ተነግሮን ነበር ፣ ምን ይሻለናል ? » አለ ያሬድ ሁሉንም በመወከል ::

« ሰው ገብቷል ፣ በዚህ ላይ ይህ ሁሉ እዚህ የተሰለፈው እሳቸውን ለማነጋገር ስለሆነ ተራ ያዙና ጠብቁ » አሏቸው ተላላኪው::

« እኛ እኮ ሠራተኞች አይደለንም :: » አለ ያሬድ :: ዘበኛው ፊቱን አዞረና ተቀመጠ :: ፀጋው የሚከተለውን መጠበቅ አልፈለገም እየጎተተ ወደሰልፉ ወሰዳቸው :: ተራ ሳይደርሳቸው ወደ ግማሽ ሰዓት ያህል ጠበቁ :: አራት ሰዓት እየተቃረበ ነበር :: በመሰልቸት ላይ እንደነበሩ ቀደም ብለው የሚያውቋቸው ጥቁር ሱፍ ለባሽ ከቢሮ ወጡ :: ሲጠባበቁ የነበሩት የፋብሪካው ሠራተኞች ሰውየውን ከበቡዋቸውና የጥያቄ መአት አጎረፉባቸው :: ሰውዬው ግን ወደፊት እየተራመዱ ፣



« ለሁሉም እመለሳለሁ » የሚል ቃል ብቻ ነበር የሚወጣቸው :: ሀሰንም እንደምንም ብሎ ሊታያቸው ሞከረ :: አልረሷቸውም ::

« መጣችሁ ? እመለሳለሁ ፣ ጠብቁ » አሉት :: ሌላ አማራጭ አልነበረም :: መጠበቅ ነበረባቸው ::

« ለምን ይሆን ጠብቁ የሚሉን ? ጊዜያችንን ባይገሉብን አይሻልም ? » አለ ሀሰን ::

« አይ ችኩል ! አሁን ሲመለሱ ጠብቅና ፣ አሁኑኑ ሥራ ካልጀመርኩ በላቸው » አለ ፀጋው በማፌዝ ::

« ለመግባት የቸኮለ ለመውጣትም እንደዚያው ነው ፣ ደግሞ አንድ ወር ሰርተህ አሰናብቱኝ እንዳትል » ሲል ያሬድም ተናገረ ::

« ያስገቡኝ እንጂ መሰናበቱን ደግሞ አስብበታለሁ :: የተሻለ ከተገኘ በጨረታው አንገደድም » ሲል ሀሰን ለመቀለድ ሞከረ ::

« ለመሆኑ አሁን ብንቀጠር ተመላልሰን ለመስራት ነው ? ወይስ እዚሁ ለመኖር ? » ሲል ፀጋው አዲስ ሀሳብ አቀረበ ::

« እኔ እንኳን ኑሮዬና እንጀራዬ የተጣመሩ ናቸው :: እዚህ ሥራ ከያዝኩ እንጀራዬም ኑሮዬም እዚሁ ይሆናል :: አባት የለኝ እናት የለኝ ፣ ምኔ ቀረና አዲስ አበባ እመላለሳለሁ ? » አለ ያሬድ ::

« እኔስ ከቤተሰቦቼ ተለይቼ መኖር አልፈልግም ፣ በጠዋት ተነስቼ ወደ ሥራዬ ማታ እፎይ ብዬ ወደቤቱ » አለ ሀሰን ::

« እኔም ቤተሰቦቼ ቢስማሙ እዚህ መኖሩን እመርጣለሁ :: ምን ጠዋትና ማታ አንከራተተኝ ? . . . አለ ፀጋው ::

« እናንተ ሁለታችሁ እዚህ ብትከራዩ ሳይሻል አይቀርም :: እኔም ሲመሽብኝ እዚሁ አድራለሁ » አለ ሀሰን በማሾፍ ::

« እኔ እንኳን አይመስለኝም :: ቤተሰቦቼ አይፈቅዱልኝም :: ተመላልሰህ ሥራ ነው የሚሉኝ » ፀጋው የራሱን ሀሳብ በማሻሻል ተናገረ ::

« እናንተ የታደላችሁ ናችሁ ። የቤት ኪራይ ፣ የምግብ ሳታስቡ ከዚህ እንደሄዳችሁ የሞቀ ቤት ይጠብቃችኋል ፣ እኔ እናንተን ብሆን ቤትም አልከራይ ፣ ቀድሞውንም ትምህርቴን ሳልጨርስ ስራም ለመያዝ አልሞክርም ነበር ? » ሲል ያሬድ በሚያሳዝን ሁኔታ ተናገረ።

« ቤተሰብ ውስጥ መኖር ማለትኮ ሁሉም ነገር የተሟላ ነው ማለት አይደለም ። ብዙ የሚጎሉ ነገሮች አሉ » አለ ሀሰን ። በመካከሉም የሚጠበቀው ሰው ሲመጣ አየና ጨዋታቸውን አቁመው በባለጉዳይ መልክ ጠበቁ ። ሰውየው አጠገባቸው እንደደረሱ ቆም አሉና ፣ « ኑ እናንተ » ብለው ሶስቱንም ወደ ቢሮአቸው ይዘዋቸው ገቡ ። አንድ ቢጫ ፋይል አወጡ ። « አንደኛው ጓደኛችሁ ጠዋት መጥቶ የቅጥር መዘርዘር እንዲያሟላ ሰደነዋል » አሉና ፋይሉን ገለጥ ገለጥ አድርገው « ያሬድ እንዳሻው » ሲሉ ተጣሩና ቀና አሉ ። ያሬድ ከሌሎች ወደፊት ቀድሞ ቆመ ። « እኔ ነኝ » በሚል ዓይነት።

« አንተ ነህ ? » አሉና እንደገና ወደ ወረቀቱ አስተውለው ፣

« ሀሰን ሰቂር » ብለው ቀና አሉ ። ሀሰንን ተመለከቱ ።

« እንግዲህ ፀጋው አንተ የተያዝከው በተጠባባቂነት ነው ። እየመጣህ መጠየቅ ትችላለህ ። እናንተ ሁለታችሁ ግን » አሉና ፊት ለፊታቸው ባለ ማስታወሻ ደብተር ላይ የሆነ ማስታወሻ ፅፈው « ቁጥር 10 ቢሮ ሄዳችሁ አቶ ታዬ ለሚባሉ ይህን ወረቀት ስጡት ፣ የቅጥር መዘርዝሩን እሱጋ ታገኛላችሁ ፣ እንግዲህ መልካም ዕድል » ሲሉ አሰናበቷቸው ። ጓደኛሞቹ እጅ ነስተው ከቢሮ ሲወጡ በፀጋው አለመቀጠር ቅር ተሰኝተው ነበር ።

« እንግዲህ እኔ ልሂድ » አለ ፀጋው በብቸኝነት ስሜት ።

« ምነው አብረን እንሄዳለን ፣ ጠብቀን » አለ ሀሰን በጓደኝነት ስሜት ።



« እኔ እንግዲህ ብቸኛ ሥራ ፈላጊ ነኝ ፣ ወደሚቀጥለው የዕድል ቀጠሮዬ ብሰማራ ይሻላል » አላቸው ። ከዚህ በላይ ፊቱን ማየት ፈሩ ። አስገድደው ከነሱ ጋር ለማቆየት ከበዳቸው ። በሀዘን ስሜት ተሰናበቱት ።

* * *

በቢሮው ውስጥ ሁለት ሴቶችና ፣ ሦስት ወንዶች ተቀምጠዋል ። ክፍሉ ሰፋ ያለ ነው ። ከሁለቱ አንደኛዋ ሴት ታይፒስት መሆንዋን ፊት ለፊቷ የተቀመጠው ታይፕ ይናገራል ። ሁለቱ አቀርቅረው ጋዜጣ ያነባሉ ። አንደኛው ግን አንድ ቀጠን ካለ ቀይ መልከ መልካም ሰው ፊት ለፊት ተቀምጦ በወረቀት ላይ እንገቱን ደፍቶ ይፅፋል ። እነ ያሬድ ወደ ክፍሉ እንደገቡ አንደኛዋ ሴት ቀና ብላ ፣ « ምን ነበር ? » ስትል ጠየቀቻቸው ።

ሀሰን ቀረብ ብሎ የያዘውን ወረቀት እያሳየ ፣ « አቶ ታዬን ነበር የምንፈልገው » አላት ። የተባለውን ሰው በእጇ ምልክት ጠቆመችው ። ሀሰን ወደ አመለከተችው ወንበር ሄዶ የያዘውን ወረቀት ለአቶ ታዬ ሰጠው ። የተፃፈውን ከተመለከተ በኋላ ፊት ለፊት የተቀመጠውን ወጣት እያሳየ ፣ « በሉ እሱ ከጨረሰ በኋላ ትመጣላችሁ ፣ እስከዚያ ውጪ ወጥታችሁ እየተዝናናችሁ ቆዩ » አላቸው ። እንደታዘዙት አደረጉ ። ውጪ ወጥተው የኮሪደሩን ግድግዳ ተደግፈው ስለ አዲሱ ስራቸው አነሱ ።

« እንግዲህ እኔን የቀጠሩኝ እንደሚመስለኝ ለዲዛይን ክፍል ነው ፣ ማን ይለቀዋል እንይዘዋለን ፣ ትንሽ ጠርቀምቀም አድርጌ ወደ ት/ቤት እመለሳለሁ ፣ የሥራ ልምዱ ግን ጠቃሚ ነው » ሲል ደስ እንዳለው ሀሰን ለያሬድ ገለጸለት ።

« እኔ እንኳን አጠራቅሜ ልማር ብልም የሚከፈለኝ ገንዘብ ከአለት ጉርሴ የማያልፍ ነው ። ከቻልኩ ግን ኤክስቴንሽን ተምሬ

እጨርሳለሁ እንጂ ከአሁን በኋላ ሥራ ፈትቼ እራሴን ችግር ላይ ለመጣል አልፈልግም ፣ አንተ እንኳ ቤተሰቦችህ ስላሉ ምንም ወጪ አይበዛብህም ። ግፋ ቢል የምግብና የትራንስፖርት ብታወጣ ነው ።» ሲል ያሬድ የ10 ቁጥር ቢሮ በር ተከፈተ ።

« ያሬድ እንደሻው »

ተጠራና ገባ ። አቶ ታዬ ፊት ለፊት ሲደርስ « ተቀመጥ » አሉት ። ከመሳቢያ ውስጥ አንድ ጥራዝ አውጥተው ፣ « ይህ የእኛ የሠራተኛ መተዳደሪያ ህጋችን ነው ፣ አንብበህ ከተረዳህ በኋላ የስምምነት ውል ትፈርማለህ » አሉት ።

ያሬድ በትዕዛዝ መልክ የተሰጠውን ጥራዝ እያገላበጠ « አሁን እዚህ ውስጥ የእኔን ህልውና የሚፃረር ቢፃፍ አልፈልግም ይላል ብለው ነው ? ይቀልዳሉ ልበል ! የፈለገውን ቢሆን በስንት ፈተናና ውጣ ውረድ ያገኘሁትን ሥራ አልፈልግም ይላል ብለው ማሰባቸው አይገርምም » እያለ ለራሱ ሲያወራ ቆይቶ አስተካክሎ ጥራዙን አስቀመጠ ። አቶ ታዬ ወደ ያሬድ እየተመለከቱ ፣ « አንብበህ ጨረስክ ? » ሲሉ ጠየቁት ። ጥራዙን አንስተው አምስት ገፅ የያዘ ወረቀት ሰጡትና ፣ « ይህን ደግሞ ሙላ » አሉት ። የተሰጠውን የፎርም ወረቀት ተቀብሎ ሞልቶ አስረከበ ። አቶ ታዬም የተሞላውን ተመልከተው እያስቀመጡ ፣

« ሥራህን ከነገ ጀምሮ መተዋወቅ ትችላለህ ፣ ከሰሞኑ ግን እስከ አንድ ሳምንት ድረስ አራት ጉርድ ፎቶግራፎች እንድታመጣ ፣ ይህን ወረቀት ውሰድና ነገ ስትመጣ ለአቶ አድማሱ ማዴቦ ስጠው ። እሱ ተቀብሎ ሥራውን ያሳይሃል ። የተቀጠርከው ለቀለማቀለም ክፍል ነው » ሲሉ አሰናበቱት ። ሊወጣ ሲል « ሀሰን ለቂርን ጥራው» ብለው ጨመሩ ። ሀሰንም እንደ ያሬድ የተጠየቀውን ፎርም አሟልቶ ጨርሶ ተያይዘው ወደ አውቶቡስ መጠበቂያው አመሩ ። ጥቂት እንደተጓዙ አንድ ቢጫ ቀለም የተቀባ ቤት አጠገብ ሲደርሱ



ያሬድ አተኩሮ ተመለከተ ጨክኖ ሊያልፈው አልቻለም ። ምነው ምን ሆንክ ? » ሲል ሀሰን ግራ ተጋብቶ ጠየቀው ። ያሬድ ዝም አለው ።

« ምነው የምታውቀው ሰው አለ እንዴ ? » አለ ሀሰን በድጋሚ ።

« አይ ምንም አይደል » አለ ያሬድ በቀዘቀዘ ስሜት ።

ያሬድና ሀሰን አዲሱን ሥራቸውን ከጀመሩ ሦስት ሣምንታት አልፏቸዋል ። አዲሱ ሥራቸው ብዙም አላስቸገራቸውም ። በተለይ ሀሰን ከሥራውም ከሰውም ጋር ብዙ እንደቆየ ሰው ተላምዶታል ። ያሬድ ግን ከሰው ጋር ለመቀላቀል ዳተኛ ነው ። ቶሎ መልመድ ቶሎ መሰላቸትን ያመጣል የሚል ፈሊጥ ስላለው ዝግታን ይመርጣል ።

ያሬድ ሥራ በጀመረ በሣምንቱ እዚያው አቃቂ እነ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት አቅራቢያ አነስተኛ ቤት ተከራየ ። በትርፍ ጊዜው ከተማዋን ከነጉራንጉሯ በመተዋወቅ ኑሮውን መምራት ጀምሯል ። ወደ ሥራ ሲሄድ ሌላ ቅያስ መንገድ ቢኖርም ምርጫው አልነበረም ። ከዛ ይልቅ ቢጫ ቀለም ያለውን ግንብ ቤት ጎማው እንደተበላሸ አውሮፕላን አዘውትሮ ይዞረዋል ። ቤቱን ባለበ ቁጥር ፣ በሩን ባየ ቁጥር ሒሊና ፣ ወ/ሮ በላይነሽ ይላል ውስጡ ። ግን እርግጠኛ አልነበረም ። ሒሊናም ሆነች ወ/ሮ በላይነሽ እረስተውት፣ ዘንግተውት ሊሆን ይችላል ። ማን ያውቃል ? እርሱ አዲስ አበባን መርሳት ይዞ የለ ። እራሱን መታዘብ ሲጀምር « የት አውቃቸውና ነው ይህን ያህል የማስበው ? » ሀሳቡን ከራሱ ለማስወገድ ይጥራል ። በዚህ ወቅት አእምሮው ዳግም ምስላቸውን ያቀርብለታል ፤ እኒያን ጎስቋላ አሮጊት ሴት ። ምርቃታቸው ፣ የዋህነታቸውን አይረሳውም ። ሥራውን ከሳቸው ፀሎት ጋር ያስተሳስረውና በባለውለተኛነት ስሜት ያስባቸዋል ።

ያሬድ ብዙውን ጊዜ ብቸኛም ቢሆን ጓደኛም አፍርቷል ። በጣም የተቀራረበው ግን ከተሾመ ገ/እየሱስ ጋር ነው ። ተሾመ

ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ፣ መዝናናት የሚወድ ፣ በሥራው የማይቦዝንና በፋብሪካው ሠራተኞች ዘንድ መልካም ግንኙነት ያለው ሠራተኛ ነው ።

« ያሬድ ምነው ፈዘዝክሳ ፣ ተጫወት እንጂ ! ደግሞ ጠጣ ፣ መፍዘዝ ሰበግም አልበጀው » አለው ። ተሾመና ያሬድ ከአንድ ቡና ቤት ተቀምጠው በመጠጣት ላይ እንዳሉ የያሬድ ሁኔታ ግራ አጋብቶት ። « እየተጫወትኩ እኮ ነው ፤ ምነው የፈዘዝኩ መሰልኩ እንዴ ? አንዳንድ ግዜ አለ አይደል - ሀሳቤ ወደ አዲስ አበባ ይዘምትብኛል » አለው ስሜቱን ለመቀየር እየሞከረ ።

« አዲስ አበባ ሩቅ መሆኑ ነው እንዴ ? ከፈለክ ሰምን አሁን ተነስተን እንሄድም ነገ በጠዋት ከተፍ ነው » አለው ነገሩን በማቃለል።

« በሳምንቱ መጨረሻ አይሻልም ? በሥራ ቀን ይደክመናል ። ሰነገው ሥራችን ዛሬ ማረፍ ይገባናል ። »

« አይ ፍሬሽ ! ሠርተህ ሞተሃል ። እኛ ሥራ እንደጀመርን ሥራ እየሰራን እንቅልፍ እንቅልፍ ይለን ነበር ። » አጠገቡ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ብርጭቆ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጎ ባንኮኒው አጠገብ የቆመችውን አስተናጋጅ በእጁ እየጠራ

« ሂሳብ ስንት ነበር የእኔ እህት ? » ሲል ጠየቀ ።

« አንተ ጋ ሦስት ቢራ እርሱ ጋ አንድ ቢራ በጠቅላላው አራት ቢራ ፤ አስራ ሁለት ብር ነው » ስትል መሰለችለት ።

ሂሳቡን ከፍሎ ወደ ያሬድ ዞር ብሎ « በል ደመ ቀዝቃዛው ሌላ ቤት እንለውጥ ፣ ትንሽ ሞቅ ቢልህ ። »



* * *

ያሬድ አቃቂ ፋብሪካ ተቀጥሮ መሥራት ከጀመረ ስድስተኛ ወሩን ያዘ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሰንብኝት ወደ ባሕር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካና ወደ ድሬዳዋ በመሥሪያ ቤቱ ተልኮ ነበር ። በሥራው ተወዳጅነትን ፣ ከቅርብ አለቆቹና አብረው ከሚሰሩት ጓደኞቹ ዝናን አተረፈ ። ቀስበቀስ ሥራውንም ፣ ሰውንም ፣ አካባቢውንም ተዋወቀ ። አቃቂን በሚገባ አወቃት ። መዝናኛና መጠጥ ቤቶችን ባያዘወትርም ፤ መዝናናት ከፈለገ « የወንድማማቾች ቡና ቤት » ይቀሰዋል ። ቡና ቤቱ በንጽህናው ፣ በግቢው ስፋት ፣ በሙዚቃ አቅርቦቱ . . . . ብቻ ግልፅ ባልሆነለት ምክንያት ለያሬድ ተመችቶታል ። እየቆየ ሲሄድ ደግሞ በዚሁ ቡና ቤት ስለወ/ሮ አባይነሽ የቤት ውስጥ ሁኔታና ስለሕሊና ወሬ ለመስማት ቻለ ። ከዚያ ወዲህ ደግሞ « የወንድማማቾች ቡና ቤት » የራሱ ቤት እስኪመስለው ድረስ አዘውታሪ ሆነ ።

« ጠጣ እንጂ » አለው ተሾመ አስተናጋጅዋ ላይ የተከለውን ዓይኑን እያየ ።

« ምክንያቱን ባላውቅም የዝች ልጅ ነገር ይገርመኛል » አለ ያሬድ ።

« የየቷ ፣ የትርሲት? » ሲል ጠየቀ ተሾመ ።

« አዎን »

« እውነትክን ነው ፤ ታሳዝናለች ። በትምህርቷ አስረኛ ክፍል ደርሳ ነበር ፤ ምን ያደርጋል ከቤተሰቦቿ ተሰይታ ትኖራለች » አለና የትርሲትን የህይወት ታሪክ መተረክ ጀመረ ።

« ነፍሱን ይማረውና አንድ ተስፋዬ የሚባል ፍቅረኛ ነበራት። ተስፋዬ የኛ የልጅነት ጓደኛችን ነበር ። በሰፈራችን የታወቀ

የእግር ኳስ ተጫዋች ነበር ። ታዲያ ይህቺ ልጅ ከቤተሰቦቿ ጋር እያለች በጣም ይዋደዱ ነበር ። የልጅቷ አባት ቀኝአዝማች ወልደሰማያት ይባላሉ ። በጣም ክፉ ሰው ናቸው ። አሁንም በህይወት አሉ ። ልጆቻቸውን በፍርሃት የገዙ ሰማንም ግድ የሌላቸው ሰው ናቸው ። ታዲያ ይሄውልህ ይቺ ልጅ ቤተሰቦቿ ቤት እያለች ከተስፋዬ ትፀንስና ከቤቷ ወጥታ ትኮበልላለች ። ትንሽ ቀናት አዲስ አበባ ቆይታ ወደ አቃቂ መጣች ። ብዙ ችግር ደርሶባት ልጁ ይወለዳል ። ህፃኑም ጤነኛ አልነበረም ፤ ሁለት ቀን እንደቆየ ሞተ ። እሷም ወደ ቤተሰቦቿ አልተመለሰችም ። ይኸውልህ ከዚያን ጊዜ አንስታ ከቡና ቤት ቡና ቤት እየቀያየረች ትኖራለች ። እዚህ ወንድማማቾች ቡና ቤት ከመምጣቷ በፊት ሾፌሮች ቡና ቤት ትሰራ ነበር ። እዚያ እያለች የማታ ትምህርት ሰመማር ሞክራ የሥራው ፀባይ አላመቻትም ። የቡና ቤቱ ባለቤት በጣም የወጣላቸው አረመኔ ናቸው . . . » ሲል ተረከለት ።

ያሬድ የሾፌሮች ቡና ቤት ሲወራ ወደ ትርሲት እያየ ፣ « ሾፌሮች ቡና ቤት ትሰራ ነበር ነው ያልከኝ ? » ሲል እንደገና ለማረጋገጥ ጠየቀው ። ተሾመ ፈገግ እያለ « ምነው ታውቃት ነበር መሰለኝ » በማለት ያሬድን ተመለከተው ።

« ማወቅስ . . . አላውቃትም ። ሆኖም እዚያ ቤት የማውቃት አንዲት ልጅ አለች ። የሴትዬዋ ዘመድ ናት » አለ ስለ ሒሲና በማሰብ እንገቱን እየነቀነቀ ።

ተሾመ እጆቹን አጠላልፎ በመገረም ስሜት ያሬድን እየተመለከተው « የትኛዋን ዘመዳቸውን ነው ? እዛ ቤት እንደሆነ መላው ሠራተኛ ቤተሰብ ነው ሲባል ነው የምሰማው » አለው ። ያሬድ ወደ ኋላ መመለስ አልሆነለትም ። ተሾመ ጥሩ ጓደኛው ሲሆን እንደሚችል አሰበ ።



« ተሾመ አንድ ምስጢር ባማክርህ ፈቃደኛ ትሆናለህ ? » ሲል ጠየቀው ።

« እጅግ የሚያስቅ ከሆነ ንገረኝ ፤ ምክንያቱም የሚያስቁ ነገሮችን ከጓደኞቼ ጋር ካላወጋሁ በእንቅልፍ ልቤ ያባንኑኛል ። . . . አይዞህ ተናገር ስቀልድ ነው » ሲል ምስጢረኛው ሊሆን እንደሚችል በሚገልፅ ስሜት አበረታታው ። « . . . ይኸውልህ እዚህ መ/ቤት ስመቀጠር ስመጣ አንድ በዕድሜያቸው ጠና ያሉ ሴትና አንዲት ዕድሜዋ በአሥራ ሦስትና በአሥራ አራት ዓመት መሀከል የሆነች ውብ ልጅ ይህንን ሾፌሮች ቡና ቤት የሚባለውን በመፈለግ ሲንከራተቱ ሳሉ ሁኔታቸው አሳዝኖኝ አፈላለኳቸው ። ቤቱን ካገኘሁ በኋላ ወደ ሥራዬ ሄድኩ ። ከዛን ቀን ጀምሮ እኛን ሴት ሁልጊዜ በህልሜ አያቸዋለሁ ። እኚያ ባልቴት ሲያነጋግሩኝ የሞተችው እናቴ በህይወት እንደገና እንዳነጋገረችኝ ነበር የቆጠርኩት ። ከዛም ይኸውልህ ያለብዙ መንከራተት ወደዚህ ሥራ ገባሁ ። ሳስበው እኛን ባልቴት ዳግመኛ መጠየቅ ነበረብኝ ። ልጅቱም ቢሆን ሊጠይቋት የሚገባ ምስኪን እና ቆንጆ ነበረች » አለ አፉ እንዳመጣለት ።

« ምንድን ነው የምትለው ፤ አሮጊቷን ነው ልጅቷን ሰማየት የምትፈልገው » አለው ተሾመ ፍርጥም ብሎ ።

ያሬድ በጥሞና ወደ ተሾመ እያየ « እየነገርኩህ » በማለት ከፊት ለፊቱ የቀረበውን ጠርሙስ ብድግ አድርጎ ተጎነጨና መልሶ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ፣ ጠርሙሱን በእጁ እያሽከረከረ ፣

« አንተ ደግሞ ቁም ነገር ሲነግሩህ ወደ ፌዝ ትሰውጠዋለህ። አሮጊቷ እዚህ እንደማይኖሩ ቀድሞውንም ነግረውኛል ። ስለእርሳቸው ማወቅ ብፈልግም መጀመሪያ ማነጋገር ያለብኝ ልጅቷን ነው » አለው።

ተሾመ ከት ብሎ ሳቀና «ታዲያ ተረት ከማብዛት ልጅቷን. . . ሰማየት . . . አፈልጋለሁ አትልም ? ስመሆኑ ልጅቷ ፣ ልጅቷ

ከማለት ስሟ ማን ይባላል ? ይሄም ምስጢር ካልሆነ ? » በማለት ጠየቀው ::

ያሬድም ከንፈሩን ወደፊት ዡርገግ አረገና « ምንም ምስጢርነት የለውም :: የልጅቱ ሥም ሕሊና ይባላል » አለው :: ተሾመ ጮክ ብሎ « ካልጠፋ ሴት ያችን ልጋጋም ልጅ ምን አስወደደህ » አለው በማፌዝ ::

« ድሮውንስ ካንተ ጋር ማውራት የኩሽና ወሬ ነው እንጂ የዚህ ዓይነት ቁም ነገር የት ይሆንሃል ? » አለው ያሬድ በንዴት ::

የቢራውን ጠርሙስ ብድግ አደረገ :: ተሾመ የያሬድን ሁኔታ ሲያይ አቀራረቡን ወደ ቁምነገር ቀየረው :: « ምስጢርህ የጨዋታ ነበር የመሰለኝ :: እንዲህ የምር ከሆነ ከእኔ ይልቅ ዝርዝሩን የሚነግርህ ሰው አለ » በማለት ወደ ባንኮኒው መለስ ብሎ የጥሪ ጭብጨባውን አሰማ ::

« አንቺ ማነሽ . . . ንግስት » አለ ::

ባንኮኒውን ተደግፋ ተክዛ የቆመች ጠይም አፍሮ መልከመልካም አስተናጋጅ ራሷን ወደ ፊት ወርወር አድርጋ ፣

« እኔን ነው ተሼ ? » በማለት እነ ያሬድ ወደ ተቀመጡበት ባንኮኒ ተጠጋች ::

« ምን ልታዘዝ ተሼ ! » ስትል ፈገግታዋን አስቀደመች:: እጁን ሸንቀጥ ባለው ወገቧ ላይ አሳርፎ ፣ « እስቲ እባክሽን ትርሲትን ቶሎ ጥሪልኝ :: እንግዳ ይፈልጋታል » በማለት ከበስተጀርባዋ ገፋ አደረጋት :: ትርሲት አጠገባቸው ቁጭ ከማለቷ ያሬድን እያስተዋለች፣

« ዛሬ ደግሞ ለማን ልትድረኝ ይሆን ? » ስትል አንገቷን ነቅነቅ አደረገች ::



« ለሁሉም ትደርሻለሽ :: ጨዋታው ረጅም በመሆኑ እኛን ምሰይ » ሲል ተሾመ አዘዛት :: ግብዣውን ተቀብላ ተመቻችታ ተቀመጠች :: ያሬድ ወሬውን ለመጀመር ፈራ፣ ውስጡ ታፈነ ::

« ስሚ ትርሲት » ሲል ጀመረ ተሾመ ፤ የያሬድ ችግር ገብቶት ::

« ዛሬ ደግሞ የመጣው እንግዳ ያሰኘው የሾፌሮች ቡና ቤት ወሬ ነው :: በይ እንግዲህ የምታውቂውን ያለምንም ቅመም ንገሪው» አላት ::

« ምን የሚወራ ነገር አለ :: ለአራት ወራት እዛ ስሰራ ቆይቼ ስለአልተስማማኝ ወጣሁ » ስትል ከንፈሯን መጠጠች ::

« እዛ እያለሽ ከሕሊና ጋር ትገናኙ ነበር ? » ሲል ያሬድ ጠየቃት ::

« ከዛች ገገማ ጋር ምን አገናኘህ ? ኦዎ አውቃታለሁ :: የቡና ቤቱ ቁልፍ ያዥ ነበረች » ስትል ባጭሩ መለሰችለት ::

« እሺ ታዲያ በኑሮዋ ደስተኛ ነች ወይስ እንደሚባለው ወ/ሮ አባይነሽ እሷንም ያገኗታል ? » ብሎ ጠየቃት ::

« እኔን ማን አፈቀላጤ አደረገኝ ? ሄደህ አትጠይቃትም ? » በማለት ቁጣዋ ገንፍሎ ብድግ ስትል ያሬድ እጇን ይዞ « ተቀመጭ ፤ ገና አውርተን መቼ ጨረስን » አላት ቁጣዋን በማብረድ ዓይነት ::

« ምን ማውራት ያስፈልጋል ? አንተ የምድሩን ሲሉህ የቆጡን ትጠይቃለህ :: ታዲያ ስዚህ ዓይነቱ ጨዋታ ጊዜው የመሸ አልመሰለህም ? » ብላው ዳግመኛ ከተቀመጠችበት ተነሳች :: የተጋበዘችው ለሌላ ነገር መስሏት ነበር ::

« ምነው እባክህ የሠፈራችሁ ልጅ የዋዛም አይደለች ፤ ቀልድም አታውቅ እንዴ ? ለማንኛውም እንኳን ምስጢሩን አወቅን » አለ ያሬድ ::

« ይህን ያህል የሚጠቅምህ ከሆነ ለምን እግረ መንገዳችንን ገባ ብለን አንወጣም » ሲል ተሾመ ሀሳብ አቀረበ ::

« ተሼ ዛሬ ይቅርብን መሽቷል :: በዚህ ላይ መጠጥ ወላስደናል :: ሌላ ጊዜ እናድርገው :: » አለ ያሬድ በፍርሃት ውስጥ ሆኖ :: እንደ ድንገት ከሕሊና ጋር መገናኘቱ ከአቅሙ በላይ ሆነበት :: ራሱን ለማረጋጋት ጊዜ ፈለገ ::

« ካልፈለክ የራስህ ጉዳይ ፤ ግን ሁለተኛ ሕሊና ፣ ሕሊና ብለህ ስሟን እንዳትጠራብኝ » አለው ተሾመ በቁጣ ፤ ሂሳብ ለመክፈል ኪሱን እየደባበሰ ::

* * *

ዶሮ ሲጮህ የተነሳችው ሕሊና ፀሐይዋ ጎህ ስትቀድ አንሶላ በመሰብሰብ ሥራዋን ጀምራለች :: ከትራስጌዋ ሥር ለደበቀችው መጥረቢያ ማምሻውን ያጋጠማትን ነገር በማይሰማ ድምፅ ነግራዋለች:: መጥረቢያውን ባለበት ፣ ባየች ቁጥር ደግሞ የአባቷ ጥሩ ፀባይ ይታወሳታል :: መከራና ችግርን በትዕግስት ማሳለፍ ከአባቴ ያገኘሁት ሀብት ነው ብላ እራሷን አፅናንታ ነበር ከመኝታዋ የተለየችው :: የመኝታ ክፍሉን ለማፅዳት ውሃ በባልዲ ቀድታ ስትሄድ « ሕሊና ነይ ቁርስ እንብላ » ስትል አስካበች ከክፍሏ በር ላይ ቆማ ጠራቻት :: ሕሊና አልተግደረደረችም :: ባልዲውን አስቀምጣ ለቁርስ ቀረበች ::

ሁለቱ የሚገናኙት በእንደዚህ ዓይነት የዕረፍት ወቅት ነው :: በእንደዚህ ዓይነቱ አጋጣሚ ሁለቱ እንደ እኩያ ጓደኛሞች ቅሬታቸውንም ሆነ ደስታቸውን ፤ የሆዳቸውን አውጥተው ይነጋገራሉ :: ሕሊና ትናንትና ስለአጋጠማት ሁኔታ ለአስካበች በጥቂቱ ልታወራላት ፈለገች :: ሁሉንም አፍረጥርጣ ለመንገር የዚህ ዓይነቱን ጉዳይ ጀምራው ስለማታውቅ ሀፍረቷ ቀደማት ::



« ዛሬ ደግሞ ምነው ምን ሆነሻል ? ብይ እንጂ ! በእህል ላይ ማለም ጀመርሽ ? ኧረ ይሄስ አያድርስ ነው » ስትል አስካበች ከጠዋት ህልሟ አባነነቻት ::

« ትናንትና ማታ አንድ ሰውዬ አስደንግጠውኝ እስከ አሁን አለቀቀኝም » ስትል ባላወቀችው ኃይል ልትደብቅ የነበረውን ጉዳይ ጀመረች ::

« የትኛው ሰውዬ ነው ? ምን አደረገ ? » አለች አስካበች በድንጋጤ ::

« ምንም አላረጉኝም እኮ ብቻ . . . ብቻ » ልትጎርሰው ያዘጋጀችውን እንጀራ በሳህኑ ላይ መልሳ አንገቷን በሀፍረት አቀረቀረች ::

« ማነው እሱ ለመሆኑ ? » ርህራሄ ባዘለ ቁጣ ::

« የእቴቴ . . ማነው ሥማቸው ? » አለች ሁኔታውን ለማቃለል በመፈለግ ዓይነት ::

«አብዬ ጋሽዬ ? እህስ ምን አደረጉሽ . . .ተቆጡሽ እንዴ. . .»

« አይ መቆጣትስ አልተቆጡኝም :: የተቆጡት እቴቴን ነው:: ፎቴው ላይ ተቀመጭ ብለው ሳልፈልግ በግድ አስቀመጡኝ . . . » አለችና ዝም አለች :: ዓይን ዓይኗን አየች :: ቀሪውን መተረክ አላስፈለጋትም :: ተግባቡ ::

« በይ ተይው ገባኝ . . . ገባኝ . . . እሳቸው ሲለክፉ ልማዳቸው ነው » አለች አስካበች በማረጋጋት ሁኔታ :: ሕሊና ከዚህ በላይ ደፍራ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት አልቻለችም :: ከአስካበች ዘንድ ለመራቅ የበሉበትን ሰሀን አንስታ ከክፍሉ ወጣች :: በመጠኑም ቢሆን ሁኔታውን ለአስካበች በመንገሯ የሆነ ነገር ቀሏታል :: ውሎ ቢያድርም ወ/ሮ አባይነሽ የአደባባይ ምስጢር ማድረጋቸው እንደማይቀር ታውቃለች ::

የመኝታ ቤቱን ፅዳት ጨርሳ የሚቀጥለውን ለመጀመር ስታስብ በክፉል የተሰናበተው ጭንቀቷ እንደገና በውስጧ አንሠራራ ። ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ይቀራታል ። ስለውስጧ ንፅህና ቢታውቅም ይኼ ብቻውን ለወ/ሮ አባይነሽ መልስ አይሆንም ። መሸሽ ብትችል ደግ ነበር ፣ ግን አትችልም ። በግዷ ወ/ሮ አባይነሽ ፊት ቀርባ የሚጠብቃትን መቀበል አለባት ። የመግቢያውን በር ቁልፍ በፍርሃት ተሸንፎ በሚንቀጠቀጠው እጇ ለመክፈት ሙከራ አደረገች ። የህልም ትግል ያህል በዳሰሳ ከፍታ ወደ ውስጥ ገባች ። በሳሎኑ ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን በፈርጅ በፈርጃቸው ለማስቀመጥ ወንበሮችን ከቦታ ቦታ ስታንቀሳቅስ ከመኝታ ክፍሉ « ማነሽ አንቺ ?» የሚል ድምፅ ሰማች ። የቆመችበት መሬት ተከፍቶ ቢውጣት በወደደች ነበር ። ወደ መኝታ ቤቱ በር ጠጋ ብላ « እኔ ነኝ እቴቴ » ስትል በስጋት ተናገረች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ቀስ ብለው በለሰለሰ አነጋገር ፣ « አንቺ ነሽ ሕሊና » አሉና መተኛታቸውን ቀጠሉ ። ሕሊና የሚቀጥለውን ንግግር ለመስማት ጆሮዋን ወደ በሩ ጠጋ አድርጋ ቆመች ። ምንም ድምፅ የለም ። ጠበቀች ። እንቅስቃሴም ፣ የተለየ ድምፅም የለም ። እንቅልፍ አሸንፏቸው ሊሆን ይችላል ብላ ገመተች ። አባይነሽ እንደገና ተወልደው አዲስ ሰው ሊሆኑ አይችሉም አለች ለራሷ ። ይልቅስ ስቃይዋ በመራዘሙ አዘነች ። ላይቀር ነገር ቢወጣላት ፣ የሚጠብቃትን ቁርጡን ብታውቀው ይሻል ነበር ። ለማንኛውም ሥራ ሀሳቧን ይቀንሳልና ወደስራዋ ተመለሰች ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ የማይገባት ነገር ተፈጠረ ። ወ/ሮ አባይነሽ የሳሎኑን በር ከፍተው ወደሌላኛው ክፍል ዘለቁ ። ሰውነቷ መራድ ጀመረ ። ወ/ሮ አባይነሽ የገቡበትን በር እንደገና ከፍተው ወደሳሎኑ ተመለሱ ። ሕሊና እንደልማዷ እጅ ነሳቻቸው ። ክፍሉ ውስጥ ሕሊና መኖርዋን የረሱ መሰሉ ። እንቅልፍ የተጫጫነውን



ፊታቸውን እያባበሱ ከቡፌ ውስጥ ብርጭቆ አውጥተው ከሕሊና አጠገብ ከቆመ ማቀዝቀዣ ጠርሙስ ውሃ ወሰዱ ። ለሕሊና ህልም ሆነባት ። ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ስለመሆንዋ ተጠራጠረች ። ህልም ላይ መሆን አለባቸው ። እሳቸው ቢሆኑ ኖሮ ውሀ ለምን ቀጠነ ትዕዛዝ ያዥጎደጉዱ ፣ እኔንም ያተራምሱ ፣ ግራ ያጋቡኝ ነበር ። እውነትም ህልም መሆን አለበት አለች ። ምናልባት በዝምታ ስቃይዋን እያራዘሙት ቢሆንስ ? እንደሳቸው ባህሪ ከዚህም በላይ ሊያደርጉ ይችላሉ ። ሕሊና ለጊዜውም ቢሆን ከሳቸው ፊት ራቂ ራቂ አላት ። ትንፋሽዋን ብትመልስ ይሻላት ይሆናል ። ከፋቱ ፍላጎቷ ምኞት ነው ። ማነው « ደሀ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ንጣት ይገድለው ነበር » ያለው ። ከፊት ለፊታቸው ቡና ማፍላት አለባት ።

የሰውነቷ ትኩሳት ጨመረ ። ለወ/ሮ አባይነሽ ቡና ላስማፍላት የምትችልበት መንገድ ቢኖር በማለት ማሰብ ጀመረች ። ሆኖም ተደርጎ አያውቅም ። የሥራ መመሪያ ከደረሳት ቀን ጀምሮ ሌላ ሰው ለወ/ሮ አባይነሽ ቡና አፍልቶ አያውቅም ። የእውር ድንበሯን ሳሎን ቤቱን ጽጽድታ ወደ መኝታ ክፍሏ ስትሄድ ሰለሞንን አገኘችው ።

« እራሴን ከፉኛ አሞኛል እትዬን ጥራልኝ » በማለት ፊት ለፊት ካለው በረንዳ በሁለት እጆችዋ እራስዋን አስደግፋ ተቀመጠች ። አስካበች መልዕክቱ እንደደረሳት አፍታ ሳትቆይ ደረሰች ።

« ምነው ሕሊና ? እኔን ፣ እኔን ፣ አመመሽ እንዴ ? » ብላ አጠገቧ ተቀመጠች ።

« ነይ ከፀሐይ ላይ ተነሽ » ስትል ደግፋ አንስታ ወደ ክፍሏ ወሰደቻት ።

በሕሊና መታመም በጣም ካዘኑት ሰለሞን አንዱ ነበር ። ወደ ቤታቸው ለመግባት ምክንያት ለማግኘት በበሩ አካባቢ ሲያንዣብብ አስካበች እንደ ድንገት ጠራችው ።

ነው የተፈቀደላቸው ። ያም ቢሆን ሁልጊዜ አይደለም ። ጥፋት ባጠፉ ቁጥር ከት/ቤት በማስቀረት ነው የሚቀጡት ። » አለቻት ።

የአስካበች ንግግር ለሕሊና ጥሩ መሠረት ሰጣት ። ባላቸው ትርፍ ጊዜ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ትምህርቱን ለመጀመር ከሰለሞን ጋር ተስማሙ ። አስካበችም ሃሳባቸውን በመደገፍ በትርፍ ጊዜዋ የሕሊናን ሥራ ለመሸፈን በራሷ ፈቃድ ቃል ገባችላቸው ። ምሽቱ በመግፋቱ ሰሰሞን የደህና እደሩ ሠላምታውን አቅርቦ ተሰናብቷቸው ወጣ ።

« በይ እንግዲህ ሕሊና ዛሬ አንቺ በሽተኛ ስለሆንሽ አልጋ ላይ ተኚ » አለች አስካበች መሬት ላይ ያለውን የሕሊናን ፍራሽ እያስተካከለች ።

« አላደርገውም ። እኔ መሬት ላይ ነው መተኛት ደስ የሚለኝ:: አልጋ ላይ መተኛት አለመድኩም » ከአልጋ ወርዳ ፣ አስካበች የምታስተካክለውን ፍራሽ ተቀብላ ከረጢቷን ትራስጌዋ አድርጋ ቁጭ አለች ። አስካበች ተጨማሪ ክርክር ማድረግ ዋጋ የሌለው መሆኑን ተገነዘበች ። ወደ አልጋዋ ሄዳ ለመተኛት ስትመቻች የሕሊናን ሥራ አስተዋለች ።

« ይህች ልጅ ምን ደግ ቢሰሩላት ሆዷ አይገኝም ። አሁን እኮ ከዚያ ከመጥረቢያ ላለመለየት ነው ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ ፣ የአህያ ሥጋ ከአልጋ ሲሉት አመድ አሉ ፤ ሰምን እራስዋን ትበድላለች ? » አለች ለራሷ ።



* * *

ወ/ሮ አባይነሽ በአብዬ ጋሻዬና በሕሊና መካከል የተፈጠረው ሁኔታ በጣም ስላሳሰባቸው የመሰላቸውን እርምጃ ወሰዱ ። ከግል ደንበኞቻቸው ጋር የሚያቀራርብ ሥራ በወንዶች እንዲከናወን በማድረግ ሕሊናን ጨምሮ ሴቶቹን አራቁ ።

የቤቱን ፅዳት በቀን ከማከናወንና ቡና ከማፍላት በስተቀር ሕሊና በምሽት ወደትልቁ ቤት መሄዷ ቀረላት ። ይህም ለሕሊና ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ከሰለሞን ጋር ለጀመረችው ምስጢር አመቺ ሁኔታ ፈጠረላት ። ሕሊና የቅጥያ ምልክቶች ቢያስቸግሯትም የራሷን ስም በግዕዝ ደረጃ « ሀለነ » እያለች መፃፍ ጀምራለች ። በአጭር ግዜ የአባቷን ተስፋ ፣ የራሷን ምኞት እንደምትጨብጥ እየታያት ክፉና ደጉን በጸጋ ተቀብላ መኖር ጀምራለች ።

አንድ ቀን ምሳዋን በልታ ጥናት ላይ ሆና ሰለሞንን ስትጠብቀው ዘግይቶ በመምጣት የረባ ሠላምታ ሳይለዋወጡ ያልጠበቀችውን መርዶ አረዳት ።

« አሁን የመጣሁት ዛሬ ማታ መምጣት እንደማልችል ልነግርሽ ነው » አላት ።

« ምነው ምን አጋጠመህ ? » ስትል ጠየቀችው በድንጋጤ ።

« ሕሊና አትቀየሚኝ የእኔንና የአንቺን በተደጋጋሚ አንድ ላይ መሆን ወ/ሮ አባይነሽ በመስማታቸው እናቴን ጠርተው ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋታል ። ስለዚህ ነገሩ እስኪረሳ ለተወሰነ ጊዜ መራራቅ ይኖርብናል » ሲል በማሳዘን ነገራት ።

« ምን አድርጊ ነው የሚሉኝ ? እኔ ብማር አሁን ምን ይጎዳቸዋል ፣ የተሰጠኝን ሥራ እንደሆን ምንም ሳላጓድል እየሠራሁ ነው ። ለምን ሰው እንዳይማር ይፈልጋሉ ? » በማለት እንባ የሞላውን ዓይኗን በሰለሞን ላይ አሳረፈች ።

« ግድ የለም ሰለሞን እስከአሁን ላደረክልኝ ዕርዳታ ከልብ አመሰግናለሁ ። ለወደፊቱ የሚቸግረኝን እልፎ አልፎ እጠይቅሃለሁ ። አሁን እጀማመሩን ካወኩት እኔው ራሴ ፊደል ቆጠራውን ለመጨረስ እሞክራለሁ ። በኔ ምክንያት በእናትህና በአንተ ላይ ችግር ማምጣት አልፈልግም » አለችው እያለቀሰች ። ሒሊና ያሰበችው አልቀረም ። ከሰለሞን ጋር የነበራት ግንኙነት ቢቋረጥም በጥረቷ በአጭር ጊዜ ውስጥ በእጇ የገባውን ጽሑፍ ለማንበብ ቻለች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ባይፈልጉትም ፣ ሊቆጣጠሩ ቢሞክሩም ሒሊና ማንበብና መፃፍ መቻሏን ተረዱ ። ለዚህ ሁሉ ለማይፈልጉት ነገር ሆና መገኘት ዋናዋ ጠላታቸው አስካበች እንደሆነች ራሳቸውን አሳመኑ ። በዚህ ዓይነት ሌላም ነገር ሊፈጠር እንደሚችል መጥፎ ሽታ አጠናቸው ። የሚጎዳቸው ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት መፍጠን አለባቸው ። አስካበች እራሷ ቂም ልታረግዝባቸው እንደምትችል ልባቸው ያውቀዋል ።

አንድ ቀን ሒሊና ወደ ቅልቁ ቤት ተጠርታ ትሄዳለች ። ወ/ሮ አባይነሽ ትልቁ ቤት ሳሎን ፎቴ ወንበር ላይ ጉብ ብለው ይጠብቋት ነበር ። በርጩማ አምጥታ ፊት ለፊታቸው እንድትቀመጥ ያዟታል። ሒሊና ክበሩ አጠገብ ወደ ግድግዳው ጠጋ ብላ ከወ/ሮ አባይነሽ ትይዩ ተቀምጣ ሁለት እጆቿን እንደሚታጠብ ሰው እርስ በርሱ እያፋተገች መሬት መሬቱን ትመለከታለች ። ለጥሩ ነገር ሊጠሯት እንደማይችሉ በመገመት ክፉውን ነገር በትዕግስት ለመቀበል ራሷን ተዘጋጅ ትለዋለች ።

« ሒሊና ትምህርትሽ እንዴት ነው ? » አሏት ወ/ሮ አባይነሽ። ለጥያቄአቸው መልስ ሳይጠብቁ « ቸኮልሽ እንጂ እኔማ ቄስ ትምህርት ቤት እንድትገቢ እያሰብኩ ነበር ። ሆኖም የዕድሜሽ ነገር እኮ ነው ችግር የሆነብኝ ። አሁን በዚህ ዕደሜሽ ከነዚያ ህጻናት ጋር አንድ ላይ መዋሉ ላንቺም ደስ አይል ፤ እኔም አላደርገው ።



የአባይነሽ ዘመድ በዚህ ዕድሜዋ እማራለሁ እያለች ትጨማለቃለች መባል ከሞት ይቆጠራል » አሏት ለስለስ አድርገው ። ሒሊና የወ/ሮ አባይነሽ ንግግር መርዘኛ እንደሆነ ወዲያው ነበረ የገባት ። ሰው ሲጎዱ ፣ የመጣን ተረኛ ወንድ ሁሉ የግላቸው ሲያደርጉ ፣ የሉ ብቻ እንደሆኑ ሲያሳምኑ በእንዲህ ዓይነት የማሳዘን መንፈስ ነው ።

ወ/ሮ አባይነሽ የጀመሩትን ቀጠሉ ። « አሁን እንግዲህ ማን አለኝ ብለሽ ነው ? አንቺ ብቻ እኮ ነሽ ቀሪ ዘመዴ ። ሁሉም ባዕድ . . . ነገ ቀን ቢጎድልብኝ ጥሎኝ እንደሚሄድ አልጠራጠርም ።

« ሥጋ ከዘመዱ አህያ ካመዱ » አይደል ! እኔ እስከአሁን መጣፍና ማንበብ የሚችል ተቆርቋሪ ሰው በማጣቴ ይኸው የምግብና የመጠጥ ሂሳቡን እነዚያ ጋለሞታዎች እያጭበረበሩኝ ነው . . . » በማለት ከንፈራቸውን እየነከሱ ቀና ብለው ግድግዳ ግድግዳውን ተመለከቱ ።

« አሁንማ አንቺ አለሽኝ ፤ እንደ ድሮው መፈንጠዝና የፈለጉትን አስቀርተው የቀረውን ከመስጠት እንዲቆጠቡ ታደርጊልኛለሽ ። አይደለም ሒሊና ? » አሉዋት ። ሒሊና ዕውቀቷን በመጠራጠር ፣ በተለይም ማንን ጋለሞታ ብለው እንደሰደቡ ስለምታውቅ ዝም አለቻቸው ።

« ሒሊና ከእንግዲህ ወዲያ አንቺ ልጅ አይደለሽም ። እስካሁንም ችላ ያልኩ የመሰልኩት ሁሉን ነገር እንድታውቂው ብዬ ነው ። ከአሁን በኋላ የምትሰሪው ሥራ በጽዳትና በመሳለለው መሆን የለበትም ። አየሽ የኛ ዘሮች ወራዳና ቆሻሻ ሥራ አይሠሩም » አሏት። ሒሊና መልስ አልነበራትም ። በተሰላቸ ስሜት የተመረጠላትን ሥራ እስክትነገር በዝምታዋ ገፋችበት ።

« ስማሽ ? ሒሊና ከነገ ጀምሮ ሥራሽ ይህ ይሆናል » አሉና ከተቀመጡበት ተነሱ ። ሒሊናም አብራ ተነሳች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ፈገግ አሉና ወደ ሕሊና ጠጋ ብለው ለመጀመሪያ ጊዜ ትከሻዋን በአንድ እጃቸው ያዝ አድርገው በሌላው ነፃ እጃቸው ፀጉሯን ነካ ነካ እያደረጉ « ጎሽ የእኔ ይሉ ምን ጊዜም ሥጋ ሥጋ ነው ። አሁን ሁለት ቆንጆ አዳዲስ ልብስ አስቀድድልሻለሁ » ሲሉ ገለጹላት ። የአክስቷ መለወጥ ገዘፈባት ። ምን ታይቷቸው ይሆን ? ስትል ለውጡን በመልካም መንፈስ ለማየት ሞከረች ። የማይለወጥ ነገር የለም ። አክስቷም ተለውጠው ሊሆን ይችላል ።

« ምን አለበት ለዘለዓለም በሁለንተናቸው እንዲህ ለስላሳና ደግ ቢሆኑ » እያለች ከራሷ ጋር እያወራች ወጥታ አስካበች ዘንድ አመራች ። አስካበች አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብላ ምሳ አቅርባ ስትጠብቃት ደረሰች ።

« እትዬ ቆየሁ እንዴ ? » ስትል አጠገቧ ሄዳ ቁጭ አለች ።

« ለመሆኑ ምን አድርጊ ነው የሚሉሽ » አለቻት አስካበች ።

ሕሊና ፊቷ ከቀረበው ማዕድ ወደ አፏ እየላከች ፣ « ዛሬስ ተይኝ እባክሽ . . . ዝምድናችንን ስናረጋግጥና ዘራችንን ስንቋጠር ውዬ መጣሁ » አለቻት ። «ምነው በስጋነትሽ ተጠራጠሩሽ ደግሞ ?» ስትል ጠየቀቻት ። « ምን መጠርጠር ይባላል የበለጠ ማረጋገጥ ነው እንጂ » አለች ቅሬታ ባዘለ ስሜት ። ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ ሕሊና ቀጠለች፤ « እትዬ እኔ እንጃ ፍርሃት ፍርሃት አለኝ ። ይህ ሁሉ ደግነት ለጤናም አልመሰለኝም » ብላ ፊቷን በማኮሳተር ልትጎርስ የነበረውን እንጀራ ሳህኑ ላይ ተወት አድርጋ አስካበች ትከሻ ላይ ጋደም አለች ።

« ምነው ? ክፉ ነገር ተናገሩሽ እንዴ ? » አለቻት ። « ክፉማ ቢሆን ጥሩ ነበር ። ደግነታቸው ያለቅጥ በዛብኝ ፣ ልብስ አስፋልሻለሁ፤ አንቺ ወራዳ ሥራ መሥራት የለብሽም ፤ ሥጋዬ ነሽ እኮ ይሉኛል » ።



« ታዲያ ምን ችገረሽ የምትሠሪው ሥራ የልፋትሽና የላብሽ ዋጋ ነው ። ከተስፋልሽ ሥራም አትስሪ ካሉሽ ተቀምጠሽ መጽሐፍሽን ማንበብ ነው ፤ ምኑ አስጨነቀሽ ? » ሕሊናን ብዙ ነገር እንደሚያስጨንቃት ለአስካበች ማን በነገራት ! « ጋለሞታ » የተባለችው አስካበች እንደሆነች ፤ ሴራው ከሷ ጋር ለማቆራረጥ እንደሆነ ማን በነገራት ! ሕሊና ሁሉ ነገር ፍች የሌለው ቅዥት እንዲሆን ተመኘች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ያሰቡትን ፈጸሙ ። የመኝታ ቤቱን ሥራ ለፈሩቅ ሰጡ ። የሕሊና ሥራ በዋናው መጠጥ ቤት ሂሳብ ያዟን መከታተልና ከዚህ ቀደም አስካበች ትሰራው የነበረውን አጠቃላይ ቁጥጥር ያጠቃልላል ። ይህን የሕሊናን አዲስ ኃላፊነት ወ/ሮ አባይነሽ ራሳቸው ለሠራተኞቹ በግንባር ቀርበው አውጀዋል ። ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ድርጊታቸው የፈለጉትንም ያህል ባይሆን በመጠኑ ሳይሰራላቸው አልቀረም ። ድርጊቱ ለሕሊና ባይገባትም አስካበች ግን ከእርሷ ጋር የነበራትን ግንኙነት እያራቀች እየቀዘቀዘች መጣች ። እንዲያም ሆኖ ሕሊና አስካበችን ተክታ መሥራት ከጀመረች ሦስተኛ ሣምንቷን አሳለፈች ። አንድ ባለ ሦስት ብር የመኝታ ቤት ተለይቶ ተለጥቷት ከረጢቷን ተሸክማ ገብታለች ። አብዛኛውን ጊዜ ምግቧን የምትበላው በዚያው በምትሰራበት ቦታ ሆነ ።

ሕሊና በመልኳም ሆነ በአለባበሷ የደረሰች ልጅ ስለመሰለች ሰው ዓይን ገባች ። ፀጉሯን ለሁለት ከፍላ ጉንጉን ተሠርታለች ። ከደረቷ ገና ወጣ ወጣ ያሉት ጡቶቿ የለበሰችውን ልብስ ብድግ ብድግ አድርገውታል ። ከሁሉም የበለጠ ሰውን የመሳብ ኃይል ያለው በመላ ፊቷ የተሳለው ውበትዋ ነው ። በመጠጥ ቤቱ የሚገባ ደንበኛ አዲሷን ስጋ ወጣት ዓይኑን ጥሎባት ነው የሚያልፈው ። በሆነው ባልሆነው ጠጋ ብሎ ለማነጋገር የሚፈልጋትን በቀዘቀዘ ስሜት መሸኘቱን ችላበታለች ። ቀደም ሲል ከነበራት ህይወት ብዙ መጥፎ

« ምን አደርጋታለሁ ? ይህች ለካራም » ብሏት ጋቢ ለብሰው ገና በመድረስ ላይ ወደ አሉት ወ/ሮ አባይነሽ አመራ ። ሕሊና በማታውቀው ኃይል ተገፍትራ ወደ ክፍሏ ገባች ። ያየችውን ማመን አልቻለችም ። ክፍሏን ዘጋች ።

« እንዴት አድርጎ መጥረቢያውን ሊቀማት ቻለ ? » ወለሉ ላይ ተዘርግታ ፊቷ ወደ ምድር የተደፋውን አስካበችን በእጇ ነካ ነካ አደረገቻት ። ሁለቱም ክፍሉ ውስጥ እንዳሉ በሩ ተበርግዶ ተከፈተ ። የወ/ሮ አባይነሽ ግዙፍ ሰውነት ከዳር እስከ ዳር በሩን ሞላው ። ግንባራቸውን ቋጠር ፈታ እያደረጉ አስካበችን አተኩረው ሲመለከቱ ቆይተው ፣ ንዴት በርትቶባቸው ለመናገር ብዙ ጊዜ ከወሰዱ በኋላ ፣

« ጥጋብሽ ብሎ ብሎ ለዚህ አበቃሽ ፤ አንቺ ምን ታደርጊ ። እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ ! « *መጀመሪያ እንቁላል ስሰርቅ . . .* » አለ ሰውየው ! እንቡላሽን እየተጋትሽ መጥተሽ ቤቱን ስትረብሺ በትዕግስት ሳልፍሽ ነው ነገሩ የጠፋው ! እኔ ደግሞ አብረን ኖረናል ፤ ክፉና ደጉን አይተናል በማለት ሁሉን ነገር ብተው ውስታዬ ይሄ ይሁን ? ለመሆኑ ልጁ ምንሽ ላይ ደረሰ ? ለምን ለአባይነሽ ተቆረቆርክ ነው ? » ሰውነታቸውን እያውረገረጉ እጃቸውን ወገባቸው ላይ አድርገው እንደአስክስታ ወራጅ አንገታቸውን እየሰበቁ ፣

« እኮ ንገሪኝ ! ይህ ልጅ ምን አደረገኝ ነው የምትይው ? ሌት እንቅልፍ የለው ፤ ቀን እንቅልፍ የለው ። ለምን የአባይነሽ ቤት አልተዘረፈም ነው ? እንደፈለግነው እንጫወትበት ነው ? ይንጋልኝ ብቻ የአቃቂው . . . አይለመነኝ አሰራልሻለሁ » ብለው ንዴታቸውን ተወጥተው ፣ ፊታቸውን መለስ ከማድረጋቸው አስካበች ከነበረችበት እመር ብላ ተነሳች ።

« መጣሽ አንቺ ደም መጣጭ አረመኔ ! የአባቴን ሀብት ሙጥጥ አድርገሽ በልተሽ ጨረሽና እኔንም እንደሎሚ መጠሽ ፣ መጠሽ ሲበቃሽ እንደአሮጌ ቁና ልትጥይኝ ትፈልጊያለሽ ። ገብስማ



ዶሮ ፣ ጥቁር በግ ጠምዝዘሽ እየጣልሽ ሰውን ማፍዘዝ ሁልጊዜ የሚሳካልሽ እንዳይመስልሽ . . . ይሄ ደግሞ ደንደላም የወንድ አልጫ አለሁ ይበል ! ትናንት ቅማሉን አራግፎ ዛሬ ከሰው እኩል ሆነና እኩል መናገር ጀመረ ። ወይኔ አስካበች ! ድራሽ ቢስ ደሃ ምንጊዜም ውሉን አይስትም ስሚ ! » አለች አመልካች ጣትዋን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቀስራ ።

« ካለእኔ የሚያውቅ የለም ። ጉድሽን ነገ ለአደባባይ አበቃዋለሁ » ስትል ዛቻ አከለችበት ።

ወ/ሮ አባይነሽ የሚሰሙት ጉድ ከአስካበች የወጣ አልመሰላቸውም ። ጆራቸውን በመጠራጠር ወደ ግራ ወደ ቀኝ እየተመለከቱ ማረጋገጫ ፈለጉ ። . . . ከፊዘዙበት ሲነቁ ሌላ ነገር ከመስማታቸው በፊት እራሳቸውን ማግለል እንደሚኖርባቸው ወሰኑ። የፈሩትን የቆሰለ እጅ ይዘው ወደ ቤታቸው አመሩ ።

« ይቺ እርጉም ሀሳቧስ ሌላ ነበር ። እግዜር አተረፈህ ልጄ፣ የአንተ ሲገርመኝ እኔንም ወረደችብኝ እኮ ፣ ሠይጣን የተፈናጠጣት ፣ አሁን ምን ነካት ይባላል ? . . . ሁሏም አንድ በአንድ ልቅም ብላ ትወጣታለች እንጂ በአንተስ ቀልድ የለም ። የማላውቅ መሰላቸው እንጂ ለምን እንደጠመዱህ ? ለእኔ በመቆርቆርህም አይደል እንዲህ የተነሱብህ ፣ ሌላ ምናቸውን ነካህባቸው ? » አሉ ዓይናቸውን ከእጁ ላይ ነቅለው ፊት ፊቱን እየተመለከቱ ።

« እኔ ያደረኳቸው አንድም ነገር የለም ። በተለይ አስካበች ሥራዋን ከለቀቀች ወዲህ ልታናግረኝ እንኳን አትፈልግም ። ተሰብስበው እንኳን ሲያወሩ እኔ ከደረስኩ በየአቅጣጫው ይበታተናሉ። ይህች ሕሊናም ብትሆን ፊት ለፊት አትናገርም እንጂ ውስጥ ውስጡን ተንኮለኛ ሳትሆን አትቀርም ! እንደው ስራዋ ሁሉ እንደ ምስጥ ነው ። » ወ/ሮ አባይነሽ የሕሊና ሥም ሲነሳ ንዴታቸው ነፍስ ዘራ ፣

« ይቺ እከካም ፣ ዘረ ኮብላይ ፣ የዘላን ልጅ እንደው እግዚአብሔር ተቃጠይ ሲለኝ አይደለም እሺ ብዬ የተቀበልኳት ! ቆይ ለእሷም ቢሆን መድኃኒት አለኝ ። ቆይ ኧረ ቆይ እያንዳንዳቸውን የማደርገውን አውቃለሁ ፣ ነገ እዚች ቤት ጉድ ይፈላል » በማለት የነገውን ቀን በዓይነ ህሊናቸው ቅርፅ ሰጥተው አሰላሰሉ ። እስካበችን በለመዱት አቀራረብ ይቅርታ እንድትጠይቃቸው ሲያደርጉ ፣ ሕሊናም የእስካበችን ፈለግ እንድትከተል ልክ ልኳን ሲነግሯት እየታያቸው ፊታቸው ፈገግ ሲል ይሰተዋል ነበር ።

« በል ነገ ክሊኒክ ትሄዳለህ ። ለአዳርህ ህመሙ ብዙ አይሰማህም ። እንደው ግድ ሆኖ ነው እንጂ ለብርዱ እዚሁ ሳሎን አንጥፈህ ብትተኛ እወድ ነበር ። »

« ኧረ ምንም አይደለም እሜቴ ። ጨርቅ ከጠቀለልኩበት ምንም አይለኝም » በማለት ብድግ ብሎ እጅ ነስቶ ወደ ለሊት ስራው ሲያመራ ወ/ሮ አባይነሽ የፈሩቅን ቁመና ግዙፍነትና የትከሻውን ስፋት በዓይናቸው ይቃኙ ጀመር ።

እንዲህ ጥቃት በተሰማቸው ጊዜ ፤ እንዲህ ንዴት ባጋጠማቸው ቁጥር ተዳፍኖ የቆየው የወንድ እምሮት ስሜታቸው ነፍስ ዘርቶ ቅርፅ ይዞ ይታያቸዋል ። እንደአንዳች አቅበጠበጣቸው ። በደም ስራቸው እየተመላለሰ የሚበላቸውን አንዳች ስሜት የሚያሳርፍላቸውን ጠንካራ የወንድ ክንድ መንተራስ ተመኙ ። ፈሩቅን . . . ። ዘወትር ለእርድ የሚመጡትን ሰንጋዎችን እንደቀላል ነገር ጠምዝዞ ድባቅ የሚያገባ ፈርጣማ ጡንቻዎቹን ለአንድ አፍታ ቃኙ ። በዘጠኝ ዓመቱ ቆይታው በፊቱ ገጽታ ላይ የታየውን ለውጥ አጤኑ . . . የመልኩን ማማር አንድ በአንድ ሰለው .ማለፍያ ነው ብለው ወሰኑ። ለሌላው ደግሞ . . . ቀን ቀጠሮ ቆረጡ ።



« ወይ ጉድ ! አባይነሽ ሆ . . . ሆ ቁጭ ብዬ ላድር ነው ? » ብለው ዘርፋፋ ሰውነታቸውን እያንከባለሉ ወደ መኝታ ቤታቸው አመሩ ።

ሕሊና ሳታስበው የተቀሰቀሰው ፀብ እንዳበቃ የአባቷን ማስታወሻ መጥረቢያዋን አንስታ ወደ መኝታ ቤትዋ ብትገባም ፣ ይህን የአባቷ ምስል አድርጋ የምትቆጥረውን መጥረቢያ ለዚህ አንባጓሮ ምክንያት መሆኑ ዕረፍት ነስቷት ከተኛችበት ቦታ ሆና ትገላበጣለች ። በተለይ በመጥረቢያው ጫፍ ላይ ያየችው ደም ሕሊናዋን አስጨነቃት ። ትኩስ ዕንባ በአራቱም መአዘን ፊቷን እየሞቀ ትራሰዋን ሲያርሰው ከለመመን ነቃች ።

« ግድ የለም ለሊቱ ይንጋ እንጂ ነገውኑ ለወ/ሮ አባይነሽ አዲሱ ሥራዬ እንደአልተስማማኝ ተናግሬ እስካበች ወደ ቀድሞ ሥራዋ እንድትመለስ አደርጋለሁ » እያለች ስታወጣና ስታወርድ እጇን ወደ ትራሰጌዋ ለዳ የመጥረቢያውን እጀታ እያሻሸች የአባቷ መንፈስ ለጓላማዋ ዕናት እንዲረዳት ስትማጠን ድንገት ከውጪ የሰው ኮቴ የለማች ስለመሰላት አቅጣጫውን ለማጣራት ጆሮዋን ቀሰራ ስታዳምጥ ኮቴው እየቀረባት ሲምጣ ተሰማት ። ሕሊና የልቧ ትርታ ጨመረ ። እጆቿን ደረቷ ላይ አስቀምጣ ድምጿን አጥፍታ የሚሆነውን በመጠባበቅ ላይ እንዳለች ያው ኮቴ በሯ ላይ ሲደርስ ባለበት ረጋ ። በሯ ሁለት ሦስት ጊዜ ቢንኳኳም ሕሊና ደፍራ በሩን ለመክፈት ወኔው አልነበራትም ። ከጥቂት ሰዓት በፊት ያየችው ዘግናኝ ሁኔታ የሚደገም መሰሎ ታያት ። ድብደባው እንደማይቆም ስትረዳ ፣

« ማ – ማነው ? » ስትል ተነፈሰች ።

« እኔ ፈሩቅ ነኝ ። መጥረቢያውን አስገብተሻል ? አጣሁት » አላት ።

« አላስገባሁትም ። ቀድሞ ነገር እኔ የት አየሁት ? » ብላ መጥረቢያውን ወደ ሰውነቷ አጥብቃ ይዛ የሚከተለውን ስትጠባበቅ የፈሩት ኮቴ እየራቀ ሲሄድ ለማች ። ጆሮዋን በየአቅጣጫው ቀስራ መሄዱን ካረጋገጠች በኋላ መጥረቢያውን እንደታቀፈች ተጋደመች ። ፈሩት በጠዋት ተነስቶ አስካበች የተማታችበትን መጥረቢያ ፍለጋ ይንጎዳጎዳል ። ትላንት ከአስካበች ታግሎ ካስለቀቃት በኋላ የት እንዳደረሰው አሰላሰለ ። የመጥረቢያውን አድራሻ ለማወቅ አልቻለም።

« ኧረ ምንድን ነው የምትፈልገው ? ለመሆኑ እጅህ እንዴት ሲያደርግህ አደረ » አሉት ወ/ሮ አባይነሽ ። አትኩሮቱን ሁሉ በመጥረቢያ ፍለጋ ላይ አድርጎ ስለነበር የመኝታ ቤታቸውን መስኮት ከፍተው ሲያስተውሉት ልብ አላለም ነበር ።

« ተሽሎኛል እሜቴ ፣ ትላንት የተመታሁበትን መጥረቢያ እዚህ ማስደገፌ ትዝ ይለኛል ፣ ሕሊናን ብጠይቃት አላየሁም ብትለኝ ልፈልገው ብዬ ነው » በዓይኑ ወዲያና ወዲህ አማተረ ።

« የቱን መጥረቢያ ነው የምትፈልገው ? ይህች መርዘኛ የአባቴ ውርስ ነው የምትለውን ነው ? » አሉ ።

« አዎ እሱ ነው መሰለኝ ከእሷው ፤ መኝታ ቤት አውጥታ አይደል የቀሰጠመችኝ ! » አለ የተመታውን ቦታ በአንድ እጁ እያሻሸ።

« የሷ መዘዝ ነው ለካ ! ይህን መጥረቢያ አውጥተሽ ማድቤት አስቀምጪው ብያት አልነበረም ? » ቢጣል ኖሮ ይህ ሁሉ እንደማይደረስ በመገመት የፈሩትን ፊት እየተመለከቱና ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ « ግድ የለም ጠፍቶ ከሆነ አያለሁ ፤ ካለም እኔው እራሴ ነኝ ከእሳት የምማግደው » ብለው ፈሩት በቆመበት ጥለውት ወደ መኝታ ቤታቸው ገቡ ።



* * *

ያለወትሮአቸው ወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤቱ ውስጥ በጠዋት ገብተው በገንዘብ መቀበያው ባንኮኒ ተቀምጠዋል ። ንዴታቸው ከፊታቸው ላይ ይነበባል ። ሆኖም ሕሊናን አላመናጨቁም ። የተደረገውንም አንስተው አልጠየቁም ። ብቻ ዝም ብለው ተቀምጠዋል ። በሆዳቸው ነገር እያብሰለሰሉ ነበር ። ሥራ ቦታዋ ያልተገኘችው አስካበች ነበረች ። በሯ እንደ ድሮው ተዘግቷል አስካበች ግን ከነጋ ብቅ ሳትል ሠዓታት ነጎዱ ። እንደ ሕሊና ምኞት የወይዘሮ አባይነሽ ንዴት ተግ እስኪል አስካበች በአካባቢው ባትታይ ፈቃድዋ ነበር ። ዛሬ ባለመምጣቷ በጣም ደስ ብሏታል ። ጊዜው እያለፈ ፣ የምሳ ሰዓት ሲደርስ የአስካበች ድምፅ በርቀትም ቢሆን ሊሰማ አልቻለም ። ወ/ሮ አባይነሽ መቁነጥነጥ ጀምረዋል ። ከነበሩበት ቦታ ተነስተው አንድ ጊዜ ወደ በሩ ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ባንኮኒው እየገቡ የተቀመጠውን ዕቃ ወዲያና ወዲህ እያስባጠሩ ፣

« ሰምን እዚህ ተቀመጠ ?ይህ ደግሞ እዚህ ምን ይሰራል ?» እያሉ ወዲያ ወዲህ የቤቱን ሠራተኞች ሲያራውጡ ቆዩ ። ወደ ሕሊና ተጠግተው ፣ « ሂጂ እባክሽ ያቺን ሰካራም ቀስቅሻት » ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ ።

ሕሊና አስካበችን የመጀመሪያዋ ሆና ለማነጋገር ባትፈቅድም የወ/ሮ አባይነሽን ቃል መፈጸም አለባት ። አስካበች የተኛችበትን ክፍል ሄዳ በሩን ቀስ ብላ ደጋግማ አንኳኳች ። መልስ ስታጣ ጊዜ « እትዬ ! እትዬ ! » እያለች ትጣራ ጀመር ። ምንም መልስ የለም።

« እኔ ሕሊና ነኝ ! እቴቴ ይፈልጉሻል ክፈቺ ብትልም ፣ በሩ ሊከፈትላት አልቻለም ። ወ/ሮ አባይነሽ በሕሊና መቆየት ተናደው አጠገቧ እንደደረሱ « የለችም እንዴ ? ለምንድነው የማትከፍተው? » ሲሉ በጥርጣሬና በድንጋጤ ዓይነት ጠየቋት ።

« መኖር አለች ። በሩ ከውስጥ ነው የተቀረቀረው ። መልስ ግን የለም » አለቻቸው ።

« ፈሩቅን ጥሪልኝ » አሉና ወደ አስካበች በር ተጠግተው ባላቸው ኃይል ደጋግመው ደበደቡት ። መልስ የለም ። ከሒሲናና ከፈሩቅ ሌላ ሌሎችም የቤቱ ሠራተኞች በበሩ አካባቢ ራቅ ብለው ቆመው ሁኔታውን መመልከት ጀመሩ ። ሁሉም በሩ ተከፍቶ ሁለቱ ሴቶች ፊት ለፊት ሲገናኙ ማየት ይፈልግ ነበር ። የቻሉትን ያህል ቢሞክሩም በሩን የሚከፍት ጠፋ ። ቀስ በቀስ ግቢው በሰዎች ተወረረ። ሀሳብ ሰጪ በዛ ። ግማሹ በሩ ይሰበር ፣ ለጤና አይደለም ሲል ፣ ሌላው መስኮቱ ይሰበር ይላል ። በመጨረሻ ወ/ሮ አባይነሽ ፈሩቅን ፣ « ስበረው » ብለው ትዕዛዝ ሰጡት ። ፈሩቅ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ከብዙ ልፋትና ትግል በኋላ በሩን በረገደው ። ክፍሉ ወለል ብሎ የያዘውን አሳየ ። መሬት ሳይነካ በሥሩ የተንጠባጠቡት ቀያይ ፈሳሽ ምልክቶች ያልተጠበቁ ነበሩ ። ይህን ጉድ ከማየቱ ፈሩቅ ጩኸቱን ለቀቀው ። ግቢው በጩኸት ተዋጠ ። ሒሲና የተንጠለጠለውን የአስካበችን አስከሬን እንዳየች ተዝለፍልፋ ወደቀች ።

« ምነው ይቅርታ በጠየኳት »



* * *

በሚያዘወትሩበት የመዝናኛ ቤት ናቸው ያሬድና ተሾመ ። አጠገባቸው ትርሲት ነበረች ። ተሾመ ዓይኑ እንባ እያቀረረ ፣ « ለመሆኑ ዘመድ የላትም እንዴ ? ከወ/ሮ አባይነሽ ሌላ ? » ሲል ጠየቀ ። ትርሲት ከንፈሯን መጠጠችና « ምን ዘመድ ይኖራታል ! ከልጅነቷ ጀምሮ ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ነበር የምትኖረው ። ጉልበቷን መጠጡና ሒሲና ስትመጣ ዓይንሽን ለአፈር አሏት እንጂ » አለች ። በሒሲና ላይ መፍረዷ ነበር ። ያሬድ የሒሲናን ሁኔታ ቀደም ብሎ ከትርሲት ተረድቷል ። አስካበችን ተክታ ዕድሜዋን ሙሉ የወ/ሮ አባይነሽ ሠራተኛ ትሆን ዘንድ እንደተፈረደባት ገባው ። ይህን በመናገር ለሒሲና ሊከራከር አልፈቀደም ።

« ይቺ አስካበች የተባለችው ሴት ለመሆኑ ምኝ ናት እንዴ ? ጥሉ መሄድ እያለ እራሷን እንዴት ትሰቅላለች ? » አላት ትርሲትን።

« ሰውማ ወ/ሮ አባይነሽ ናቸው ያስገደሏት እያለ ያማል » ያሬድ እራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ፣ « በምን ምክንያት ሊያስገድሏት ይችላሉ ? መቼም የሆነ ምክንያት መኖር አለበት » አለ ።

ትርሲት እጇን ወደ ላይ አንስታ « የሚነግዱትም ሆነ ለቤታቸው የሚያውሉት እህል ከአስካበች አባት መሬት ነው አሉ የሚመጣው ። አስካበች በአደራ የተሰጠቻቸው ልጃቸው ነበረች ። በኋላ ግን አባቷ ሲሞቱ መሬቱን በስማቸው አዛውረው በሴትየዋ ነፍስ መጫወት ጀመሩ » አለች በሚያሳዝን ቅላፄ ።

« ህግ ባለበት ሀገር ምንድን ነው ችግሩ ? ለምን አይከሷቸውም ? » ሲል ያሬድ ጠየቃት ። « አንተ አታውቃትም ! አባይነሽ እኮ በዚህ ሀገር ንጉስ ነች ፣ ማን እሷን ይከሳል ? » አለ ተሾመ ከትርሲት ቀድሞ ።

* * *

በዋናው ቤት የከተማው ሰው ተሰብስቦ ወንበርና መሬት ላይ በተነጠፈው ፍራሽ ላይ ተቀምጦ በሹክሹክታ ያወራል ። ከሰሩ ፍራሽ፣ መካከል ላይ ብርድ ልብስና ከላይ አልጋልብስ በተነጠፈበት ሰፍራ በርከት ያሱ ሴቶች ከመካከላቸው አንዲት ወፍራም ሴት ከበው ያስተዛዝናሉ ። የተወሰኑ ራሳቸውን ገለል አድርገው የግል ጨዋታቸውን የያዙም ይታያሉ ። አስተናጋጆች አስር ጊዜ እየተነሱ ለአዳዲስ ለቀስተኞች ኮካኮላ ፣ ቡና ፣ ንፍሮ በእንቅብ ለማቅረብ ይጣደፋሉ ። የቸኮለ ወይም መሄድ የፈለገ ወደ ትልቋ ሴት ቀረብ ብሎ ማዘኑን በመግለጽ እጅ ነስቶ ይወጣል ።

ተሾመና ያሬድ እንደሌሎቹ ሁሉ እጅ ነስተው ተያይዘው ከትልቋ ሴት ትይዩ ካለው መቀመጫ ላይ አረፍ አሉ ። አንድ መልከ መልካም ረዘም ያለች ሴት ልጅ እነያሬድ ከተቀመጡበት አካባቢ ፈገግ ብላ እንቅብ መሳይ መሶብ አቀረበች ። ተሾመ ያሬድን አትኩሮ እያየ ከንፍሮው ዘገነ ።

ያሬድ መላው ሰውነቱ ደንዝዞ በደመነፍስ ወደአቀረበችው ንፍሮ እጆቹን ዘረጋቸው ። ዓይኖቹ ግን ከልጅቷ ፊት ላይ ተንከራተቱ « ሕ - ሊና አወቅሽኝ ? » አላት ለሷ ብቻ በሚሰማ የሹክሹክታ ድምጽ ። ሕሊና ለአፍታ ዓይኖቿን አጥብባ ከተመለከተችው በኋላ ከመቅጽበት የፊቷ ገጽታ ተለዋወጠ ። ግራና ቀኙን ተገላምጠች ። በተለይ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ አቅጣጫ በመላቀቅ ቀስ ብላ ተመለከተች ። ወ/ሮ አባይነሽ ሊያስተዛዝኑዋቸው ከመጡ የሰፈሩ ሴቶች ጋር ጨዋታ ይዘዋል ።

ፊቷን ወደያሬድ መለስ አርጋ እያየችው « አውቄሃለሁ ። » ግን እንዴ . . ት ልትመጣ . . . » አላስጨረሳትም ። « ገባኝ ገባኝ ስላንቺ የኑሮ ሁኔታ ሁሉንም ባላውቅም የተወሰኑ ነገሮችን ግን



አሰማለሁ ። በስራዬ ምክንያት እዚሁ አቃቂ እናንተው አካባቢ ቤት ተከራይቻለሁ ። » አላት እሱም እንደሷ ለጋት ይዞት ።

ሁኔታዎች አመቺ ባለመሆናቸው ብዙ ሊያነጋግራት አልቻለም። የወ/ሮ አባይነሽ ጐረቤቶች እግዜር ያጥናችሁ በማለት አንድ በአንድ መውጣት ጀምረዋል ። ያሬድ ከዚህ በኋላ መቆየቱ ፋይዳ እንደሌለው ስለተገነዘበ ሕሊናን በርቺ በማለት እጆቹን ለስንብት በመዘርጋት አጥብቆ ጨበጣት ። ሕሊና እነያሬድ ተርታ ላሉ ሰዎች ከንፍሮው ካስዘገነች በኋላ እንገቷን ደፍታ ወደመጣችበት ተመለሰች።

ያሬድና ተሾመ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቀረብ ብለው አንገታቸውን ዝቅ በማድረግ እግዜር ያጥናችሁ በማለት ተሰናብተው ወጡ ። ጥቂት እንደተራመዱ « የማይታመን ሰውጥ ነው ። ይህን ያህል ሰውጥ ይኖራታል ብዬ መገመቱ ይከብደኛል ። እንኳን አንድ ቀን ያያት አብሯት ያደገ ይለያታል ብዬ ለመገመት ይቸግረኛል ። » አለ ያሬድ እራሱን በመገረም እየነቀነቀ ።

« እሱን ተወውና ከእንግዲህ ምን ቀረህ ? መነጋገራችሁ መልካም ነው ። አለመርሳቷም ይገርማል ጥሩ የማስታወስ ችሎታ አላት » አለው ተሾመ ያሬድን የጎሪጥ እያየው ።

« እባክህ ተሼ አታፊዝብኝ እኔ ልጅቷን ሳይሆን . . . በማን ልማልልህ – የእናቴን ሥጋ ነው የምልህ ፤ እኛን ባልቴት . . . »

* * *

የአስካበች ድንገተኛ ሞት የወይዘሮ አባይነሽን ቤት ሀዘንና የፖሊስ ምርመራ አናጋው ። ንግዱ ቀዝቀዝ አለ ። ወ/ሮ አባይነሽ ሀዘኑን በትልቁ ቤታቸው ተቀምጠው ሰባቱንም ቀን ሳይነሱ አሳለፉ ። ነገር ግን የፖሊስ ምርመራው አስክሬኑ ከተገኘበት መኝታ ቤት አንስቶ በቤት ውስጥ ከአስካበች ጋር ግንኙነት አላቸው የሚባሉትን ሰዎች ሳይቀር ቃላቸውን እንዲሰጡ ተደርጎም አልቀመም ። ወ/ሮ አባይነሽ ፖሊስ ጣቢያ ደርሰው የሚመጡትን የቤት ሠራተኞቹን ሁሉ እያስጠሩ ጥያቄ ያቀርቡላቸዋል ። እራስዋን መግደሏ ሳይሆን ያስጨነቃቸው ራስዋን ለመግደል ያበቃትን መንስዔ ነበር ። ለአስካበች ህይወት ማለፍ ምክንያት የወ/ሮ አባይነሽ ድርጊት መሆኑን ራሳቸው ሳይጠረጥሩ አልቀሩም ። አስካበች ከመሰቀሏ ቀደም ብሎ በተፈጠረው ሁኔታ የተናገሩት ነገር ተደብቆ የኖረን ምስጢር በጥቂቱም ቢሆን ይፋ ሳያደርግ አልቀረም ። በዚህ ምክንያት የቤት ሠራተኞቹ ነገር አሳስቧቸዋል ። ሠራተኛ የሰማው ነገር ክንፍ አውጥቶ ይበራል ይባላል ።

ወ/ሮ አባይነሽ ሰው ሸሹ ። ሰው በተሰበሰበበት መታየቱን ጠሉ ። የግድ ሆኖባቸው እንጂ ሀዘኑን ባጭሩ በመቅጨት ብቸኛ ለመሆን ፈልገው ነበር ። ሰው በገባና ሀዘኑን በገለፀ ቁጥር የራሳቸው ሁኔታ እያሳዘናቸው ያለቅሳሉ ። ፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው ቃላቸውን የሰጡ ቀን ምንም ሳይናገሩ ወደ መኝታ ክፍላቸው ገብተው ሰው ሳያዩ ቀኑን ሙሉ ውለው ነበር ።

ሕሊና በአስካበች ሞት ከልቧ አዝናለች ። ይህን ትፈጽማለች ብላ አልጠበቀችም። ግፋ ቢል በስካሯ ትቀጥላለች የሚል ግምት ነበራት ። የእሷን ስራ መልሶ መስጠትና ወደ ቀድሞ ሥራዋ



መመለስ መፍትሄ ነው ብላ አስባ ነበር ። ሳይታሰብ አስካበች እራሷን አጠፋች ። ባሰበቻት ቁጥር አልቅሽ አልቅሽ ይላታል ።

« ለምን ታለቅሻለሽ ? » የሚላት ግን የለም ። ወ/ሮ አባይነሽ ብቻ የሕሊና ያን ያህል መሆን እየከነከናቸው ፣ መኝታ እየነሳቸው መጣ ። የማያውቁት ነገር ወለወሳቸው ። ሕሊና ከመምጣቷ በፊት ከአስካበች ጋር ሠላም ነበሩ ። እሷ ከመጣች በኋላ ግን በመጀመሪያ ሆድ ለሆድ ተራራቁ ፣ ቀጥሎ ተጣሉ ፣ በመጨረሻም እራሷን አጠፋች ። ቤታቸው ተበጠበጠ ። መጪውን ማሰብ አልፈለጉም ። ይኸ ሁሉ የሆነው ግን ሕሊና ከመጣች በኋላ ነው ።

« ይህች ገሬ ዘመዶችዋን ሁሉ ጨርሳ እኔንም ልትጀምረኝ ነው ? » አሉና ካለችበት አስጠሯት ። አጠገባቸው እንደቀረበች ስለመጥረቢያው ነበር ያነሱባት ። መጥረቢያው ከአባቷ የወረሰችው ማስታወሻ እንደሆነ በመግለጽ አሁንም ከእሷ ጋር መኖሩን ነገረቻቸው።

« አባትሽ ይህን መጥረቢያ ከየት ነው ያመጣው ? » ሲሉ አፋጠጧት።

« ከገበያ ገዝቶ ነዋ ! » ስትል በፍርሃትና በጥርጣሬ መለሰች።

« እሱስ አይደለም . . . የደብተራና የቃልቻ ሥራ መሆኑን መቼ አጣሁት » አሉና በውስጣቸው ፣ « አሁን ታዲያ መጥረቢያው ምን ያደርግልሻል ልጄ ? » በማለት ጠየቋት ። ሕሊና ይህንን ነበር የፈራችው ዓይኗን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ አፍጥጣ « በቃ የአባቴ ማስታወሻ ነው ። » አለቻቸው ።

« ጅል ነሽ ልበል ። ከመቼ ወዲህ ነው መጥረቢያ የአባት ማስታወሻ ሆኖ የሚያውቀው ፣ ፎቶ አይደል . . . በይ አምጪውና፣ ማድቤት ይቀመጥ ፣ ቦታው እዚያ ነው » አሏት ።

« እቴቴ ምንም ቢሆን የአባቴ ቅርስ ስለሆነ ይተውልኝ ። ምናልባት ቀስ እያልኩ እረሳው ይሆናል ። እስከዚያው ግን

ይተውልኝ ፧ እርሶን መቼም አይጎዳዎትም » ስትል ተሰማመጠቻቸው ። አፈጠጡባት ። አፈ ሠፊ አውሬ መስሰው ታይዋት አፈገፈገች ።

*　　　*　　　*

ሕሲና ከቤት ስትወጣ በአንድ አሮጌ ጨርቅ የጠቀለለችውን አስር ብር ይዛ ነበር የተነሳችው ። የወ/ሮ አባይነሽን ዋናውን በር ወጣ እንዳለች ሁሉም ነገር ቀልሎ ተሰማት ። . . . ሞት . . . ፍርሀት . . . ጭንቀት . . . ከዚያ ችግር ካሳለፈችበት ቤት ስትወጣ የነፃነት ትርጉሙ እየገባት ነበር ። ግን ደግሞ ወደዬት እንደምትሄድ አታውቅም ። ከወ/ሮ አባይነሽ እጅ ማምለጡ በቂ እንዳልሆነ መረዳት ስትጀምር ፍርሀት ሸው አለባት ። ቢሆንም ወደኋላ መመለስ የለም ። ራሷን ማጠናከር ይሻላታል ። ምሽቱን ራሷን አረጋግታ ለማሳለፍ ወሰነች ።

ከከተማው ወጣ እንዳለች ማደሪያ ስትቃኝ « ወንድማማቾች ቡና ቤት » የሚል ፅሁፍ ጠራት ። በጓሮ በር በኩል ቀስ ብላ ገባች።

« መኝታ አለ ? » በሩን የከፈተላትን ዘበኛ ጠየቀች ። እሱም ሕሲናን መልከት አድርጎ በእጇ ያንጠለጠለችውን ከረጢት በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከተ « ባለስንት ? » ሲል ጠየቃት ።

« ባለሁለት ወይም ባለ ብር ከሃምሳ » አለችው ።

ወደ መኝታ ክፍል ኃላፊዋ ወሰዳት ። የመኝታ አከራይዋ በቦታው አልነበረችም ። አለበት ቆሞ ጮክ ብሎ « ትርሲት . . . ትርሲት ! አንቺ ትርሲት » እያለ ተጣራ ። በዚህ ጊዜ ጨለማ የመሰለው ፊቷ ወገግ እያለ ፤ እየፈካ መጣ ። አንዲት መልኳ የማያስከፋ አጠር ያለች ጠይም ሴት ወደቆሙበት እየመጣች ፤

« አለቀባችሁ እንዴ ? ዛሬስ ገቢያችን እንዴት ደርቷል ? » ብላ « ባለስንቱን ነው የምትፈልጊው ? » አለቻት ልብ ብላ ሳታያት።



« እንደምን ውለሻል ትርሲት ? ባለአምስቱን እስቲ ልየው » አለች ሕሲና ዕቃዋን ብድግ እያደረገች ። ትርሲት ሥሟ ሲጠራ ቀና ብላ ለማየት ሞከረች ። ዓይኖችዋን ተጠራጠረች ። ግራ ተጋባች ። « ሰ . . ሰ . . ሰ . . ራስሽ ነው ወይስ ሰለው ነው የምትፈልጊው ? ውጪ ማደር ጀመርሽ እንዴ ? ጎሽ ልጄ እንዴት አማረብሽ » በወቀሳ ዓይነት ከሕሲና እጅ ከረጢቱን ተቀብላ ወደ መኝታ ክፍል እያመሩ ።

« ይሄ ደግሞ ምንሽ ነው ? » አለቻት የከበዳትን ከረጢት መሬት ላይ አሳርፋ ። ዓይን ዓይኗን እየተመለከተች መልስ ስታጣ « አባረሩሽ እንዴ ? » አለቻት ። ሕሲና እንባ ያቀረረውን ዓይኗን ትርሲት ላይ ተክላ ፤ « እኔው እራሴ ወጣሁ » ስትል መለሰችላት ። በሁኔታዋ እጅግ ያዘነችው ትርሲት እነሱ ከሚተኙበት አልፎ ያለውን ክፍል አከራይታት መጣሁ ብላት ወጣች ።

የትርሲትና የሕሲና ትውውቅ የጀመረው በወ/ሮ አባይነሽ ቤት ነበር ። ድሮ እንዲህ አልጋ ፈላጊ ሳትሆን የመጠጥ ቤት ኃላፊ ሆና ትርሲት አስተናጋጅ ነበረች ። ከአለካበች ጋር በፈጠረችው አምባጓሮ ከቀን ወደቀን ፀቡ እየከረረ ስለመጣና ስለተማረረች ቤቱን ለቃ ወደሌላ መሸጋገሩን መረጠች ። ይህ ለትርሲት ቀላል ነበር ። መደበኛ ሥራዋ ስለሆነ አልከፋትም ።

ሕሲና ትርሲትን በማግኘቷ በአንድ በኩል ደስ ሲላት በሌላ በኩል ምስጢር ይባክናል በማለት መፍራቷ አልቀረም ። ብዙ ላለማውራት ወሰነች ። የትርሲት እንደ ድንገት መውጣት ደግሞ አላሰባት ። ሮጣ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ለመናገር የሄደች መሰላት ። በጣም ተሸበረች ።

« አንቱ ! አንቱ ጋሼ ! » ብላ ተጣራች ። ከቡና ቤቱ ጓሮ በር አጠገብ የቆመውን ብርድልብስ የለበሰ ዘበኛ ። « እባክዎት ትርሲትን ይጥሩልኝ » አለች በልመና ዓይነት ። አብሮት ካለው ካኪ ለባሽ ጋር በከባድ ወሬ የተጠመደ የሚመስለው ዘበኛም ፤

ተግተልትለው ወደክፍሉ ዘለቁ ። ወ/ሮ አባይነሽን አየቻቸው ። መዓቱን ያወርዱታል ። ሁሉም ነገር ግልፅ ሆነላት ።

« ና ጠፍርልኝ እባክህ » አሉ በትእዛዝ መልክ ። ሕሊና ሁሉንም ነገር በንቀት ነበር የተመለከተችው ። ፖሊሶቹ አንደኛው ሕሊናን ሌላኛው የሕሊናን ከረጢት ያዙና ወ/ሮ አባይነሽን አስከትለው እየተንደረደሩ ከቡና ቤቱ ወጡ ። ፖሊስ ጣቢያ እንደደረሱ ከረጢቱን የያዘው ፖሊስ ሕሊናን እንደያዛት ገንጠል ብላ ወደምትገኘው አነስተኛ ወደሆነች ቤት አመሩ ። ፖሊሱና ሕሊና ተከታትለው ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ሕሊና ከረጢቷን አስመዝግባ ስትጨርስ « ተከተይኝ » አላት ፖሊሱ ። ጥቂት እርምጃዎች እንደተራመዱ በፊት ከገቡበት ቤት ሠፋ የሚል ክፍል ውስጥ ይዟት ገባ ።

ሕሊና የክፍሉን ዙሪያ በዓይኖቿ አማተረች ። ክፍሉ የዝምታ ድባብ ተጭኖታል ። ሁሉም ነገር በስርአቱ ተቀምጧል ። መዝረክረክ አይታይበትም ከግድግዳው በስተቀኝ በኩል አስር አለቃ አለነ ከደረቱ ለጠጥ ብሎ ተቀምጧል ። በቀኝ እጁ በብእሩ ጫፍ ጠረጴዛውን ያንኳኳል በክፍሉ ውስጥ የሚሰማው ብቸኛ ድምጽ የብእሩ ኳኳታ ነበር ። አንገቷን አቅንታ ወደመርማሪው ፖሊስ ስትመለከት በድፍርስ ዓይኖቹ በፌዝ ያያታል ።

እጆቹን ጠረጴዛው ላይ በማስደገፍ ፊቱን ወደ ሕሊና ለገግ አድርጎ « አንቺ ነሽ እህ . . ገንዘብ ተቀባይ ? » ከእግር እስከራስዋ አስተዋላት ፤ መርማሪው ።

ወ/ሮ አባይነሽ በሩን ሞልተው ከውጭ ሲገቡ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀበሏቸው ።

« ይቺ እኮ ነች » አሉና በጥላቻው ጫፍ ወደ ሕሊና እያመለከቱ ፤ « ምሽላቃ ሌባ » በማለት የስድብ ናዳቸውን አወረዱባት ።



የ፲ አለቃ አለነም በተለመደ ዘዴው ማስፈራሪያዎችንና ዛቻዎችን አወረደባት ። « መች አጣኋት ፤ አውቃት የለም እትዬ » ሲል ወገናዊነቱን አሳየ ። ከሌሎች እስረኞች ጋር እንዲቀላቀሏት ተደርጎ ወ/ሮ አባይነሽና የ፲ አለቃ ለብቻቸው ምርመራ ክፍል ውስጥ ምክክር ጀመሩ ። ለሁለት ሰዓታት ከሌሎች ሴት እስረኞች ጋር ከቆየች በኋላ እንደገና ተጠርታ የ፲ አለቃ ወደሚገኝበት ክፍል ገባች ። በሚያስፈራ ዓይኑ አፍጥጦ እየገላመጣት ፤

« አሁን የምልሽ አጭር ነገር ነው ። ወደቤትሽ ትመለሻለሽ ወይስ እዚሁ ለመበስበስ ትፈልጊያለሽ ? » አላት በኃይለ ቃል ። የመናገር ዕድል የተሰጣት መሆኑን ከ፲ አለቃው ዝምታ በመረዳት ፤

« እኔ የምመለስበት ቤት የለኝም ። የግል ሀብቴ የሆነውም በእጃችሁ ይገኛል ንብረትነቱ የራሴ ነው ። አመጥታችሁ ማየት ትችላላችሁ ። » አለች ወደ መርማሪው አስር አለቃ አለነ እያየች ። መርማሪው ትንሽ አሰብ አድርጎ ፊቱን ወደፖሊሱ መለስ በማድረግ ንብረቴ የምትለውን እንዲያመጣ አዘዘው ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፖሊሱ አንዲት አነስተኛ ከረጢት ይዞ ገባ ። ጌታዬ ቢፈቅዱልኝና እኔው በሳይዎት ስትለው መፍቀዱን አንገቱን በማወዛወዝ ገለጸላት ። ሕሊና ወደመርማሪው ቀረብ ብላ እኔ ከወ/ሮ አባይነሽ ቤት የነካሁት ነገር የለም ብላ ውስጡ ያለውን ዕቃ ወለሉ ላይ ጣለችው ።

በአድራጎቷ የተደናገጠው የ፲ አለቃ አንዳች ነገር ሳይተነፍስ ዓይኖቹን ዕቃው ላይ ተክሎ ቆየ ።

« ይህ ደግሞ ምንሽ ነው ? » ብሎ ዕቃውን በእግሩ ገፋ አደረገው።

« የአባቴ መጥረቢያ ነው ! » ስትል በአጭሩ መለሰችለት ። አጭር መልስ ስትመልስለት በራስዋ የመተማመን ስሜት ለፍኖ ታያት ።

« እኔ ወደዚያ ቤት ከዚህ በኋላ ተመልሼ አልሄድም ። ከዚህ በፊት እዚያ ቤት ተቀምጬ እራሴን ያሰጨነቅሁት ይበቃኛል » አለች ቁርጥ ባለ አነጋገር ።

* * *

« ምን ልታዘዝ » ስትል ተቅለሰለሰች ፣ ፈገግታዋን አስቀድማ ።

« ፈቃድሽ ከሆነ እኔ የምፈልገው ዳንስ ነው » አላት ሀሰን እሱም በፈገግታው አፀፋውን እየመለሰላት ።

« ግድ የለም ለሌላ ጊዜ ይሁን » አለችና « እርስዎስ ? » ስትል ጣቱን እየነከሰ ወደሚተክዘው ተጠግታ ጠየቀች ፣ ያሬድ ነበር።

« አሁን የምንጠብቀው ሰው አለ ፣ ከምናመላልሰሽ ቢመጣ አይሻልም እመቤት ? » ሲል አክብሮት በተሞላው ዓይነት ከላይ እስከታች ወጣቷን ዳሰሳት ።

« ያንተው ይሻላል » ስትል እንደሕፃን ልጅ መሬቱን ዳስ ዳስ እያደረገች ወደ ባንኮኒዋ ተራመደች ። ትዕግስታቸው በማለቅ ላይ ነበር ተሾመ ሲመጣ ። ከኋላው ትርሲትን አስከትሏል ። ተሾመ ፊት ላይ የመደናገጥ ስሜት ይነበብ ነበር ።

« ያሬድ ና ጉድህን ስማ » አለውና እጁን ጎትቶ አስቀመጠው።

« ምንድን ነው ጉዱ ? »

« አሳሰሯት እኮ » ስትል ወሬውን ትርሲት ጀመረች ።

« ወ/ሮ አባይነሽ መቼ ነው . . . እቴ ? . . እዎ ከሦስት ቀን በፊት ሕሊና ትታቸው ስትወጣ ጊዜ ሀብቷን ዘርፋለች በማለት ከሁለት ፖሊሶች ጋር እዚህ መጥተው ይዘዋት ሄዱ ። » የያሬድ ፊት በድንጋጤ ተለወጠ ። « ቆይ እንደዚህ አይደለም ፣ እኛም



እንቀመጥ፣ ሀሰንም ይስማው » አላቸው ። ሀሰን ወደተቀመጠበት ወንበር ተያይዘው ሄዱ ። ትርሲት ከሦስት ቀን በፊት ስለተፈጠረው ድርጊት ፣ ስለሕሊና መታሰር ዘርዝራ አስረዳቻቸው ። በመጨረሻም « ይኸውላችሁ አሁን መሄጃ ጠፍቷት ፖሊስ ጣቢያ በቆይታ ትገኛ ለች » አለች ።

ያሬድ የተሰማውን ስሜት መደበቅ አልቻለም ። ባይነ ህሊናው ወገን አልባ ፣ ምስኪንና ጥገኛ ሕሊናን ፣ እና ጎስቋላዋን ባልቴት አሰበ ። በአውቶቢስ ተሳፍረው ወደ አቃቂ አብረው የመጡበትን ሁኔታ አስታወሰ ። በተለይ በተለይ ለቅሶ ቤት የተለዋወጡት ጥቂት ቃላቶች ትህትናዋ ፣ ፍርሃቷ ፣ ታወሰው ። እንዳች ኃይል ገፋው በፍጥነት እርምጃ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አመራ ።

በያሬድ ሁኔታ የተደናገጡት ሀሰንና ተሾመ ተከትለውት ሄዱ። ያሬድ የፖሊስ ጣቢያውን ሥነ ሥርአት ተከትሎ ሕሊና ላደረሰችው ጥፋትና በደል በኃላፊነት ሊጠየቅ ዋስትናውን አረጋግጦ ሕሊና በቆይታ ወዳለችበት ክፍል በፖሊስ አጃቢነት አመራ ። ሀሳቡ ተበተነ ራሱን ለሕሊና እንዴት እንደሚያቀርብ አብሰለሰለ ። ከጥቂት የሀሳብ ውጣ ውረድ በኋላ በመጀመሪያ ደረጃ ከአሥር ማስፈታት ብሎም ቀጣዩን እንደአመጣጡ ለመመለስ ወሰነ ። ስሜቱ እይሉ ድርጊቱን የተሻማው ፊቱ የቆመችውን ሕሊናን ሲያይ ነበር ። በሁኔታው ግራ የተጋባችው ሕሊና እጇን አጣጥፋ በእርሷና በያሬድ መሃከል ያለውን ፖሊስ በዝምታ ተመለከተች ።

ያሬድና ሕሊና ለአፍታ ትኩረታቸው አንድ ሆነ ። ስሜታቸውን ለመግለጽ ቋንቋ አላስፈለጋቸውም ። አንዱ በሌላው ፊት ላይ የተሳለውን ተናበው በመረዳት ባሉበት ቆመው ቀሩ ።

« ሕሊና ያጋጠመሽን ሰማሁ አይዞሽ » ያለው ያሬድ ቅስሙ እንደተሰበረ በሁኔታዋ እንዳዘነ ተመስጦ ነበር ። ዕንባ ያቆረዘዙት የሕሊና ዓይኖች የደረሰባትን በደልና ብቸኝነት ቢያመላክቱም ፣ ዝግ

